## ምዕራፍ ፡ ፻፺፯ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ፖርቱጋል ፡ አጭር ፡ ታሪክ ።

፩ ፤ ፖርቱጋል ፡ ያለው ፡ በእስጳንያ ፡ ምዕራብ ፡ ነው ። በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ከአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ ይዋሰናል ። የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ አራት ፡ ሚሊዮን ፡ ይሆናል ። ዋናው ፡ ከተማ ፡ ሊዝበን ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነው ። ወይንና ፡ ዘቢብ ፡ ፖርቱካንና ፡ ሎሚ ፡ ለማግኘት ፡ አያሎች ፡ መርከቦች ፡ እየጐበኙት ፡ ያልፋሉ ።

፪ ፤ ፖርቱጋል ፡ አየሩ ፡ በፍጹም ፡ እንደ ፡ እስጴን ፡ ነው ። ሕዝቡም ፡ ቢሆኑ ፡ እስጳኞችን ፡ ሲመስሉ ፡ በቋንቋቸው ፡ ልዩ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ፖርቱጋል ፡ ጥንት ፡ የእስጳንያ ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ነበረና ፡ በአገሩም ፡ ላይ ፡ በሚ ሆነው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይታሰባል ። ባሥራ ፡ ሁለተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በራሱ ፡ አዳሪ ፡ ሆነ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የእስጳንያ ፡ ዜጋ ፡ ቢሆን ፡ የተለየና ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ።

፬ ፤ ፖርቱጋሎች ፡ በመርከብ ፡ በአትላንቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ መሄድ ፡ ሲጀምሩ ፡ እስከ ሺ ፡ ፬፻ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ የፖርቱጋሎች ፡ ታሪክ ፡ ትንሽ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ በጣም ፡ አልታወቀም ፡ ነበር ። ማንም ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ ለመሻ ገር ፣ ወይም ፡ አፍሪካን ፡ በመርከብ ፡ ሆኖ ፡ ለመዞር ፡ የደፈረ ፡ ሰው ፡ አንድም ፡ አልተገኘም ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ታናናሾቹ ፡ የፖርቱጋል ፡ መርከቦች ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እየራቁ ፡ ሄዱና ፡ በመጨረሻው ፡ ከብዙዎቹ ፡ አንዲቱ ፡ መርከብ ፡ መልካም ፡ ተስፋ ፡ ወደ ተባለው ፡ አገር ፡ ለመድረስ ፡ በቃች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የፖርቱጋል ፡ መርከብ ፡ ፈጽሞ ፡ አፍሪካን ፡ ዞሮ ፡ አለፈና ፡ የህንድ ፡ ውቅያኖስን ፡ ተሻግሮ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ አገር ፡ ደረሰ ።

፮ ፤ ይህም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ድፍረትና ፡ ሌላ ፡ አገርን ፡ ማግኘት ፡ ሌሎችን ፡ ነገ ዶች ፡ አስቀናና ፡ ወዲያው ፡ ከጥቂት ፡ ዘመናት ፡ በኋላ ፡ ክሪስቶፎር ፡ ኮሎምቡስ አሜሪካን ፡ አገኘ ። እስከ ፡ ሺ ፡ ፬፻፺፪ ፡ ዓ. ም. ለኤውሮጳና ፡ ለእስያ ፣ ለአፍሪካ ፡ ሕዝብ ፡ ያልታወቀውን ፡ የምዕራብን ፡ ሰፊ ፡ የብስ ፡ ለማግኘት ፡ መንገድ ፡ መሪ የሆነው ፡ ፖርቱጋል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ።

፯ ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፯፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ድረስ ፡ በፖርቱጋል ፡ የሆነ ውን ፡ መናገር አያስፈልገኝም ። መላውን ፡ ከተማ ፡ ሊዝበንን ፡ የሚያናውጥ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ቤቶች ፣ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፣ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ ሁሉ ፡ በድንገት ፡ እየተናዱ ፡ ተከመሩና ፡ ፍራሽ ፡ መስለው ፡ ይታዩ ፡ ነበሩ ። ምድሩ ፡ እየተሠነጠቀ ፡ አፉን ፡ ከፈተ ። ስንትና ፡ ስንት ፡ ቤቶች ፡ እየተ ናዱ ፡ በዚያ ፡ ተከተቱ ። መጀመሪያ ፡ ባሕሩ ፡ እየዋለለ ፡ ከፊቱ ፡ ያገኘውን ፡ እየ ጠራረገ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ በሚያስፈራ ፡ ሁኔታ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ የሚሆኑ ሰዎች ፡ ሕይወታቸውን ፡ አጡ ።

፰ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ በዓለም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ አያሎች ፡ የቅኝ ፡ አገሮች ፡ መሥርተዋል ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ የቅኝ ፡ አገር፡ በሺ፡፰፻፯ ፡ ዓ. ም. የፖርቱጋል፡ ንጉሥ ፡ ከነ፡ቤተሰቡ ፡ የተመላለሰበት ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ፡ብራዚል፡የተባለው፡ አገር ፡ ነው ። ይህም ፡ የተባለበት ፡ ምክንያት ፡ ፈረንሳይ ፡ ፖርቱጋልን፡ እየወረረ፡ ስለ ፡ አስቸገረ ፡ ነው ።

፱ ፡ በሺ፡፰፻፰፡ ዓ. ም. እንግሊዝና፡ፖርቱጋል ፡ ፈረንሳይን፡አስወጡና ፡ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የፖርቱጋል፡፡ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። እርሱም ፡ ከሞተ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ዘውዱ ፡ ትግል ፡ ነበር ። በመጨረሻው ፡ ዶና ፡ ማሪያ ፡ የተባለች፡ በዙፋኑ ፡ እንድትቀመጥ ፡ ነገር ፡ ተጨረሰ ። ይህችም ፡ በሺ፡፰፻፶፫ ፡ ሞተችና፡ ልጅዋ ፡ ፔድሮ ፡ ፭ኛ ፡ በስፍራዋ ፡ ተተካ።እርሱ ፡ በሺ፡፰፻፷፩ ፡ ሲሞት፡ ወንድሙ ሉዊስ ፡ ፩ኛ ፡ ኅዳር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ሺ፡፰፻፷፩ ፡ ዓ. ም. በዙፋኑ ፡ ተቀመጠ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ የፖርቱጋል ፡ ወሰን ፡ ዳርቻው ፡ እንዴት ፡ ነው፡ ? የሕዝቡስ ፡ ብዛት ፡ ? ዋናው፡ ከተማ ፡ ማነው ፡ ? ሊዝቦን ፡ ከሎንዶን፡ በየት፡አኳያ ፡ ነው፡ ? ከማድሪድስ፡ ? ሊዝቦን ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፡ ፖርቱጋል ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው፡ ? ሕዝቡስ ፡ ቋንቋቸውስ ፡ ?

፫ ፡ ፖርቱጋል ፡ እንዴት ፡ ሆነ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ነጻ ፡ ወጣ፡ ? ከ፲፱ኛው ፡ መቶ፡ ዓመት ፡ ወዲህ ፡ ፖርቱጋል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፬ ፡ ከሺ፡፬፻፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ፖርቱጊዞች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? በዚሁ ፡ ዘመን ፡ የአትላንቲክ ፡ ባሕር ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፭ ፡ የፖርቱጋሎች ፡ መርከቦች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? እንደምን ፡ ተገኙ ፡ ?

፮ ፡ የተገኙትን ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ምን ፡ አደጋ ፡ አገኛቸው ፡ ? እስከ፡ሺ፡፬፻፺፪፡ አሜሪካ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፯ ፡ በ፲፯፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ምን ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ? ስለ ፡ መሬት ፡ መናወጥ ፡ ተናገር ።

፰ ፡ የፖርቱጋል ፡ ቅኝ ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? የፖርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
ወደ ፡ ብራዚል ፡ ለምን ፡ ሄደ ፡ ? የሄደውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፱ ፡ ከዚህ፡በኋላ፡ምን፡ተከተለው፡ ? የቀድሞው ፡ ንጉሥ ፡ ማን፡ይባላል ፡ ?

## ምዕራፍ ፣ ፳፪ ፣ ኤውሮጳ ።

### የፈረንሳይ ፣ ሁኔታ ፣ ስለ ፣ አየሩና ፣ ስለ ፣ ከተሞች ፣ ስለ ፣ ተግባረ ፣ እድ ።

### የሕዝቡም ፣ ጠባይና ፣ ልማድ ።

፩ ፤ ፈረንሳይ ፣ ያለው ፣ በኤውሮጳ ፣ ምዕራብ ፣ በኩል ፣ ነው ። የሕዝቡ ፣ ቍጥር ፣ ፴፱ ፣ ሚሊዮን ፣ ይሆናል ። ዋናው ፣ ከተማ ፣ ፓሪስ ፣ እጅግ ፣ ታላቅ ፣ ከተማ ፣ ነው ። ዙሪያው ፣ በደንጊያ ፣ ተገንብቶ ፣ በብዙ ፣ ምሽግ ፣ ተመሽጓል ። እጅግ ፣ ጥሩ ፣ ጥሩ ቤቶች ፤ ባደባባዩ ፣ ያማሩ ፣ አታክልቶች ፤ ያማሩ ፣ መተላለፊያ ፣ መንገዶችና ፣ ጐዳናዎች ፤ በጣም ፣ ደስ ፣ የሚያሰኙ ፣ የመጫወቻ ፣ ስፍራዎች ፣ ሁሉ ፣ መልተውበታል ። ለማንም ፣ እንግዳ ፣ ሆኖ ፣ ለመጣ ፣ ከሌላ ፣ ይልቅ ፣ ይህ ፣ እጅግ ፣ የሚስማማ ፣ ከተማ ፣ ነው ።

፪ ፤ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ከፓሪስ ፣ በቀር ፣ ሌሎችም ፣ ያማሩ ፣ ብዙ ፣ ሰፋፊ ፣ ከተሞች ፣ አሉ ። ከነዚሁም ፣ መኻከል ፣ ሩን ፣ ያማረ ፣ ፈርጥና ፣ የከበረ ፣ ደንጊያ ፣ የሚሠራበት ፣ ነው ። ሊዮንስ ፣ ጥሩ ፣ ሐር ፣ የሚወጣበት ፣ ነው ። ማርሴል ፣ ሕዝቡ ፣ ወይን ፣ የሚሸጡበትና ፣ የሚነግዱበት ፣ ነው ። ቦርዶ ፣ ባገሩ ፣ መኻከል ፣ ወይንና ፣ ሌላም ፣ መልካም ፣ ፍሬ ፣ የሚገኝበት ፣ ነው ።

፫ ፤ የፈረንሳይ ፣ አገር ፣ አየሩ ፣ ፍጹም ፣ እንደ ፣ አሜሪካ ፣ ነው ። ፔንሲልቫኒያን ፣ ሜሪላንድንና ፣ ቬርጂኒያን ፣ ይመስላል ። መሬቱ ፣ ፍሬያም ፣ ነው ። ላገሩ ፣ ሕዝብ ፣ የሚበቃ ፣ ምግብ ፣ ይሰጣል ። አገሩ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ ፍሬ ፣ ቼሪስ ፣ (እንጆሪ) ፣ ፔርስ ፤ ኮክና ፣ በለስ ፤ ሌላም ፣ ይህን ፣ የመሰለ ፣ ሁሉ ፣ ይሰጣል ። ደግሞ ፣ ልክ ፣ የሌለው ፣ ወይን ፣ ያፈራል ። ከዚህም ፣ የተመረጠ ፣ ልዩ ፣ ዐይነት ፣ ነቢት ፣ ይሠራሉ ።

፬ ፤ ፈረንሳይ ፣ አገሪቱ ፣ መላዋ ፣ ትክክል ፣ ሜዳ ፣ ናት ። በሰሜንም ፣ ሆነ ፣ ወይም ፣ በደቡብ ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ መሬት ፣ አይገኝበትም ። ወደ ፣ መኻከሉ ፣ አዳጋ ፣ ስፍራ ፣ የሚባለው ፣ ከባሕር ፣ በላይ ፣ ከፍታው ፣ ከ፫ሺ ፣ ፊት ፣ አይበልጥም ። ያገሩ ፣ ሁኔታ ፣ መልካም ፣ ሆኖ ፣ ይታያል ። ዳሩ ፣ ግን ፣ በሳርዲኒያና ፣ በእስፓንያ ፣ ዳርቻ ፣ አንዳች ፣ ነገር ፣ ያልበቀለባቸው ፣ ከፍ ፣ ያሉ ፣ ተራሮች ፣ ይታያሉ ።

፭ ፤ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ የሚገኙ ፣ ታላላቅ ፣ ወንዞች ፣ ሴን ፤ ሎይር ፤ ጋሮንና ፣ ሮን ፣ ናቸው ። ፈረንሳይ ፣ መልካም ፣ የሆኑ ፣ ወደቦች ፣ (የመርከብ ፣ መቋሚያ) ፣ አሉዋት ። ከነዚህም ፣ ዋኖቹ ፣ እሊህ ፣ ናቸው ። ደንኪርክ ፤ (ካሊስ) ቡሎንገር ፤ ዳይፕ ፤ ሀቭር ፤ ካየን ፤ በእንግሊዝ ፣ ካናል ፣ ጠረፍ ፣ ያለ ፣ ሴንት ፣ ማሎ ፤ ብሬት ፤ ናንትስ ፤ ሮኬል ፤ ሮክፎርት ፤ ቦርዶና ፤ ባዮን ፤ በቢስኬ ፣ ባሕር ፣ ጠረፍ ፤ በማርሴሌም ፤ በሜዴቴራኒያንም ፤ ቱሎን ፤ ቸርቡርግ ፤ ብሬስት ፤ ሮክፎርት ፤ ሎሪየንት ፤ ቱሎን ፣ እነዚህ ፣ ሁሉ ፣ የፈረንሳይ ፣ ዋኖች ፣ የታወቁ ፣ የመርከቦች ፣ መቋሚያ ፣ ስፍራዎች ፣ ናቸው ።

፮ ፤ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ እጅግ ፣ ጥቅም ፣ ያለው ፣ ተግባረ ፣ እድ ፣ በብዙ ፣ ስፍራ ፣ ይሠራል ። ሕዝቡ ፣ ፈርጥና ፣ ሐር ፤ ታላቅና ፣ ትንሽ ፣ ሰዓት ፣ ሌላም ፣ የጌጥ ፣ ነገር ፣

ሁሉ ፡ በመሥራት ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ እየተሠራ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ይላካል ። ምንም ፡ እንኳ የማያስፈልግ ፡ ቢሆን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሁሉ ፡ ይቀበላቸዋል ።

፲፯ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ልብስ ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ። ዘመን ፡ አመጣሹን ፡ ልብስና ፡ አለባበስ ፡ ለዓለም ፡ የሚናኙት ፡ በፓሪስ ፡ ያሉት ፡ ልብስ ፡ አሰናጂዎች ፡ ናቸው ። ከነገሥታት ፡ ይልቅ ፡ በከተማው ፡ ያሉ ፡ የሴቶችን ፡ ቀብና ፡ ቀሚስ ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ተከታይ ፡ አላቸው ። የኤውሮጳና ፡ የአሜሪካ ፡ ሴቶች ፡ የለበሱት ፡ የራስ ፡ መሸፈኛና ፡ ልብስ ፡ የተሠራው ፡ እነርሱ ፤ ባወጡትና ፡ ባመለከቱት ፡ ሁኔታ ፡ ነው ።

፲፰ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ። ምንም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሰነፎችና ፡ አሳብ ፡ እንደሌላቸው ፡ ቢቈጥሩዋቸው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፡ ፈረንሳይ ፡ አያሌዎች ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ አፍርታለች ። ያገሩም ፡ ታሪክ ፡ እጅግ ፡ የተመሰገነ ፡ ሥራ ፡ አሳይቶአል ።

፲፱ ፤ መጀመሪያ ፡ ደስታ ፡ ፈላጎች ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፡ ብላችሁ ፡ ታስቡዋቸው ፡ ይሆናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ልብ ፡ አድርጋችሁ ፡ ጠባያቸውንና ፡ ጨዋታ ፡ ወዳጆች ፡ የመሆናቸውን ፡ ታሪክ ፡ ብትመረምሩ ፡ እንዲህ ፡ በመሆናቸው ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ዕውቀት ፡ ለመመርመር ፡ የሚያቅታቸው ፡ ወይም ፡ አሁን ፡ እንደሚታየው ፡ ለአገራቸው ፡ ራሳቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ለማቅረብ ፡ የማይችሉ ፡ ናቸው ፡ የሚባሉ ፡ አይደሉም ።

<u>ጥ ያ ቄ</u>

ፈረንሳይ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ወሰኑስ ፡ ? ፈረንሳይ ፡ ከእስጳንያ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ከእንግላንድ ፡ ? ከዩናይትድ ፤ እስቴትስ ፡ ? ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ትሄዳለህ ?

፩ ፤ የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ስለ ፡ ፓሪስ ፡ ተናገር ። ከማድሪድ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ሩን ፡ ሊዮን ፡ ምንድናቸው ፡ ? ማርሴል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ቦርዶ ፡ ምንድነው ፡ ?

፫ ፤ ፈረንሳይ ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? መሬቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ፍሬ ፡ ይሰጣልን ፡ ?

፬ ፤ አገሩ ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ?

፭ ፤ ዋና ፡ ዋኖቹን ፡ ወንዞችንና ፡ ጠረፎችንም ፡ ንገረን ፡ ?

፮ ፤ የፈረንሳይ ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ምንድነው ፡ ?
በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ የሚሠሩት ፡ የሚያሥቁ ፡ ምናምንቴ ፡ ዕቃዎች ፡ ለምን ፡ ይጠቅማሉ ?

፯ ፤ ስለ ፡ ልብስ ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የሴት ፡ ቆብ ፡ ቀሚስ ፡ የሚሠሩ ፡ እንዴት ፡ ያደርጋሉ ፡ ?

፰ ፤ የፈረንሳዮች ፡ ጠባይ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? ታሪካቸው ፡ ምን ፡ ያሳያል ፡ ?

፱ ፤ የጦርነት ፡ አካሄዳቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፳፫ ።

### ስለ ፡ ጎሎችና ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ተባሉት ፡ ነገድ ፡

### መጀመሪያ ፡ በደቡብ ፡ ኤውሮጳ ፡ ክፍል ።

### በኋላ ፡ ደግሞ ፡ በሰሜን ፡ ክፍል ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡

፩ ፤ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ተባሉት ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኤውሮጳ ፡ ሕዝብ ፡ በዚህ ፡ ታሪክ ፡ እየመላለስሁ ፡ ለማመልከት ፡ ምክንያት ፡ ነበረኝ ። ስለ ፡ ነርሱም ፡ የተሻለ ፡ አሳብ ፡ ልሰ ጣችሁ ፡ ከሁን ፡ የተሻለ ፡ ጊዜ ፡ አላገኝም ። በኤውሮጳ ፡ ክፍል ፡ እየገቡ ፡ ከተሰራ ጩት ፡ ከሌሎቹ ነገዶች ፡ በፊት ፡ ግሪኮች ፡ በኤውሮጳ ፡ ገብተው ፡ ስፍራ ፡ መያዛ ቸውን ፡ ልብ ፡ ሳታደርጉት ፡ አትቀሩም ። የመጀመሪያዎቹ ፡ ባላገሮች ፡ ነገደ ፡ ያፌት ናቸው ። እነዚህም ፡ በግሪክና ፡ ፊቀቅ ፡ ብለው ፡ በኤውሮጳም ፡ ክፍል ፡ ተበታት ነው ፡ ስፍራ ፡ ያዙ ።

፪ ፤ እነዚህም ፡ በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ ጠረፍ ፡ እየበዙ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ በሜዴቴራንያን ፡ ዙሪያ ፡ ባለው ፡ ጠረፍ ፡ ሁሉ ፡ አገሩን ፡ እያቀኑ ፡ እንዲይዙ ፡ የሚበቃ ፡ ሕዝብ ፡ ሰደዱ ። እኩሌቶቹ ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ረግተው ፡ ቈዩ ። እኩሉም ፡ በኢጣልያና ፡ በእስ ጳንያ ፡ ተቀመጡ ። እነዚህም ፡ አገሮች ፡ ለጤና ፡ የሚስማሙ ፡ ሙቀት ፡ ያላቸውና ፡ ያማረ ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጡ ፡ ሁነው ፡ ስለ ፡ አገኙዋቸው ፡ በዚያ ፡ እየተባዙ ፡ በፍጥነት ፡ ባላገሮች ፡ ሁነው ፡ ቀሩ ። በጠረፉ ፡ ሲኖሩ ፡ ብዙ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩዋቸውና ፡ ወደ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ እየቀዘፉ ፡ ይነግዱ ፡ ጀመር ።

፫ ፤ እንደዚህ ፡ በማድረግ ፡ ከብዙ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ሀብታሞች ፡ ለመሆን ፡ በቁ ፤ በለ ጠጉ ። ከዚህ ፡ ወዲያም ፡ ሰፊ ፡ ከተሞችና ፡ ያማሩ ፡ ቤቶች ፤ ቤተ ፡ ጣዖቶችና ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ ይሠሩ ፡ ጀመር ። አሁን ፡ ታሪካቸውን ፡ በነገርኋችሁ ፡ አገሮች ፡ በደ ቡብ ፡ ኤውሮጳ ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታው ፡ ይኸው ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ሆነው ፡ ሲኖሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገድ ፡ እየተሰደዱ ፡ በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ በኩል ፡ በብ ዙው ፡ ክፍል ፡ ገቡበት ።

፬ ፤ በዚህ ፡ በኩል ፡ አገሩ ፡ ብርዳም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መሬቱ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ አይሰጥም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ኤልክ ፤ ሬንዲር ፤ ፎሎዲር ፡ የሚባሉ ፡ ሌሎችም ፡ ሮበክ ፡ የዱር ፡ ወይፈኖች ፡ የዱር ፡ ዓሣሞች ፡ ሌሎችም ፡ አውሬዎች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ለባላገሮቹ ፡ ምግብ ፡ ሆኑዋቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለሚያድኑ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ ሲሳይ ፡ ሆነው ላቸው ፡ ነበር ።

፭ ፤ በዚህ ፡ አውራጃ ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ ሰው ፡ አልገባበትም ፡ ነበርና ፡ መሬት ፡ ርካሽ ፡ ነበር ። የሚመጡት ፡ ሁሉ ፡ መሬት ፡ ለመያዝ ፡ ይችላሉ ። የዚህም ፡ ወሬ ፡ እየተ ሰማ ፡ በለስላሳውና ፡ በመልካሙ ፡ አገር ፡ የነበሩት ፡ ከግሪክ ፤ ከኢጣልያ ፤ ከእስጳኝ ፤ ከእስያ ፡ እየፈረጠጡ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ገሠገሡ ።

፯፡ አንዱ ፡ ጅንስ ፡ አንዱን ፡ ሲከተል ፤ አንዱ ፡ ነገድ ፡ ሌላውን ፡ ነገድ ፡ ሲከተል ፡ ከደቡብ ፡ ሜዲቴራኒያን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሰሜን ፡ አርክቲክ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ አገሩ ፡ ሁሉ ፡ ተያዘ ። በአሜሪካም ፡ የሆነው ፡ እንደዚሁ ፡ ነበር ።

፰፡ መጀመሪያ ፡ አውሮጶች ፡ የአሜሪካንን ፡ ክፍል ፡ ሲይዙ ፡ አስቀድመው ፡ የአንትላንቲክን ፡ ጠረፍ ፡ ያዙና ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቤት ፡ መሥራትንና ፡ ከተሞች ፡ መመሥረትን ፡ ጀመሩ ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የአደን ፡ አውሬና ፡ ሰው ፡ ያልያዘው ፡ መሬት ፡ እንፈልጋለን ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ውስጥ ፡ መሄድ ፡ ጀመሩ ። እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ እየገፉ ፡ ገቡ ። እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እስኪደርሱ ፡ መግፋታቸውን ፡ አላቆሙም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩፡ ግሪክ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፪፡ በሜዲቴራኒያን ፡ ጠረፎች ፡ ያሉት ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?
በዚያ ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፫—፬፡ በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ መሬቱና ፡ አየሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ያሉት ፡ እንደምን ፡ ይኖራሉ ፡ ?
ሕዝቡ ፡ በምን ፡ ይኖራሉ ፡ ?

፭፡ መሬቱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ለመኖር ፡ ሕዝቡን ፡ የሚያጓጓቸው ፡ ምንድነው ፡ ?

፮፡ ሕዝብ ፡ አሜሪካ ፡ መግባቱን ፡ ተኤውሮጳው ፡ ጋራ ፡ ብናበላልጠው ፡ እንዴት ይሆናል ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### የአራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ታሪክ ፡ ይቀጥላል ።

፩፡ ከደቡብ ፡ ኤውሮጳና ፡ ከእስያ ፡ በየጊዜው ፡ የፈለሱት ፡ ሕዝብ ፡ የሰሜን ፡ ኤውሮጳን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ያዙት ፡ እነሆ ፡ አሳየኋችሁ ። እነዚህንም ፡ ባገሩ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሕዝብ ፡ ጢም ፡ ብሎ ፡ እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ እያደር ፡ እየሰፋ ፡ እንደሚሄድ ፤ መጕረፉንም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ሰፊ ፡ ውሃ ፡ ምላት ፡ እንመስላቸዋለን ።

፪፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳትረሱ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ እነዚህ ፡ ስደተኞች ፡ ውጊያ ፡ የሚወዱ ፡ አሕዛቦች ፡ ነበሩ ። እያንዳንዱ ፡ ነገድ ፡ ጅንሱንና ፡ ወገኑን ፡ ጠብቆ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ ታላቅ ፡ ነገድ ፡ መሆን ፡ አይፈልግም ፡ ነበር ፤ በቍጥር ፡ እየበዙ ፡ ሲሄዱ ፡ እንዲሁም ፡ በኀይል ፡ ይበረቱ ፡ ነበር ።

፫፡ ጥቂት ፡ ቈይተው ፡ ሁለት ፡ ነገዶች ፡ ቅርብ ፡ ለቅርብ ፡ ሲሆኑ ፡ በመኻከላቸው ፡ ጦርነት ፡ ይነሣ ፡ ጀመር ። የበረታ ፡ ጦርነትም ፡ ሆነ ፤ ብዙዎችም ፡ በጦርነቱ ፡ ይሞታሉ ።

አንድ ፣ አንድ ፣ ጊዜም ፣ አንዱ ፣ ነገድ ፣ በጭራሽ ፣ ይጠፋል ፤ ወይም ፣ ሁሉም ፣ ይገደላሉ ። ደግሞም ፣ በባርነት ፣ ይገዛሉ ። እለዚያም ፣ ካገር ፣ አስወጥተው ፣ ያባርሩዋቸዋል ።

፬ ፤ ነገሩ ፣ ባጭሩ ፣ መጀመሪያ ፣ በአሜሪካ ፣ ነጮች ፣ በገቡ ፣ ጊዜ ፣ እንደሆነው ፣ እንደ ፣ አሜሪካን ፣ እንዲያን ፣ ነው ፤ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ልዩነት ፣ ነበር ። በሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ ያሉ ፣ አራዊት ፣ ሕዝብ ፣ ብዙ ፣ ብልሀት ፣ ይዘው ፣ የመጡ ፣ ናቸው ። የጦር ፣ መሣሪያቸውም ፣ ጋሻና ፣ ጦር ፤ ጐራዴም ፣ ነበር ፣ እንጂ ፣ ቀስትና ፣ ፍላፃ ፣ ብቻ ፣ አልነበረም ።

፭ ፤ ከባላገሮቹ ፣ ይልቅ ፣ እነርሱ ፣ የተሻለ ፣ ቤት ፣ ነበራቸው ። ይህ ፣ ሁሉ ፣ ሲሆን ፣ ተናዳጅ ፣ ሕዝብ ፣ ነበሩ ። በብዙ ፣ ነገርም ፣ እንደ ፣ አሕዛብ ፤ ሲያባርሩ ፣ እንደማይመለሱ ፣ እንደ ፣ ዱር ፣ ዓሣማና ፣ እንደ ፣ አንበሳ ፣ ናቸው ።

፮ ፤ ከነዚሁ ፣ ከሰሜን ፣ ነገዶች ፣ በጣም ፣ የታወቁት ፣ ስመ ፣ ጥሩዎቹ ፣ መጀመሪያ ፣ በፈረንሳይ ፣ አገር ፣ ባላገሮች ፣ የሆኑ ፣ ጎል ፣ ወይም ፣ ኬልት ፣ የተባሉት ፣ በጀርመን ፣ አገር ፣ የገቡት ፣ ፍራንክና ፣ ሱቪ ፣ የተባሉት ፤ በኖርዊና ፣ በስዊድን ፣ በላፒላድ ፣ የገቡትና ፣ በኋላም ፣ በጀርመንና ፣ በሁንጋሪያ ፣ የገቡት ፣ ሁንስ ፣ የተባሉት ፣ ናቸው ። አሁን ፣ ሁሉን ፣ ለመንገር ፣ አያስፈልግም ፣ እንጂ ፣ ሌሎችም ፣ አያሎች ፣ ነገዶች ፣ አሉ ።

፯ ፤ መላው ፣ የሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ በነዚህ ፣ አራዊት ፣ ሕዝብ ፣ እንደ ፣ ተያዘ ፣ ልብ ፣ አድርጉት ። ይልቁንም ፣ ጊዜያቸውን ፣ በአደንም ፣ በጦርነትም ፣ በሌላም ፣ ጠንካራ ፣ ነገር ፣ እያሳለፉ ፣ ደፋሮችና ፣ ጐበዞች ፣ ሆኑ ። ወገናቸውም ፣ እየበዛ ፣ ኀይለኛ ፣ ነገድ ፣ ለመሆን ፣ በቁ ።

፰ ፤ ስለ ፣ ሆነ ፣ መቸውንም ፣ ቢሆን ፣ ዕረፍት ፣ የላቸውም ። እንደ ፣ አውሬም ፣ ናቸው ፣ የሚፈልጉትን ፣ ነገር ፣ በትጋት ፣ ይመለከቱታል ፤ ባገኙትም ፣ ጊዜ ፣ ዘለው ፣ ቶሎ ፣ ብለው ፣ ይወጡታል ፤ እንዲሁም ፣ እነዚህ ፣ አራዊት ፣ ሕዝብ ፣ ብዙ ፣ ሀብት ፣ ወደ ፣ አለበት ፣ ከተማና ፣ ለም ፣ ወደሆነው ፣ አገር ፤ ወይን ፣ ወደሚገኝበትም ፣ ወደ ፣ ደቡብ ፣ ኤውሮጳ ፣ ዐይናቸውን ፣ ጣሉ ።

፱ ፤ በዚያን ፣ ጊዜም ፣ የሮም ፣ መንግሥት ፣ ሊወድቅ ፣ ይንገደገድ ፣ ነበር ፤ የሮሞችም ፣ ጦር ፣ እነዚህን ፣ ለማስፈራራት ፣ አልሆነለትም ። ፬፻ ፣ ዓመት ፣ ሲሆን ፣ በጣልያኖች ፣ አገር ፣ ሜዳ ፣ ላይ ፣ የጦር ፣ ሠራዊታቸውን ፣ ማጉረፍ ፣ ጀመሩ ። አላሪክ ፣ የጎቶች ፣ ንጉሥ ፣ ሮማውያንን ፣ አስገበራቸው ። ደግሞ ፣ አቲላ ፣ የሁንስ ፣ ንጉሥ ፣ ይህችኑ ፣ ከተማ ፣ ለማጥፋት ፣ አምሳ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ አስፈራራቸው ።

፲ ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ እነዚህ ፣ ዕረፍት ፣ የሌላቸው ፣ ዘራፎች ፣ መልካሙን ፣ የኤውሮጳን ፣ ክፍል ፣ እስኪይዙ ፣ ድረስ ፣ በየጊዜው ፣ የደቡብ ፣ ኤውሮጳን ፣ ከመውረር ፣ አላቋረጡም ።

፲፩ ፤ የሰሜን ፣ ኤውሮጳ ፣ አሕዛቦች ፣ መጽሐፍ ፣ የላቸውም ። ጽሕፈትም ፣ አያውቁም ፣ ብዬ ፣ እንደ ፣ ነገርኋችሁ ፣ የጥንት ፣ የታወቀው ፣ ታሪካቸው ፣ እጅግ ፣ ትንሽ ፣

ነው ። ሮምንና ፡ እስጳንያን ፡ ሌላውንም ፡ የደቡብ ፡ ኤውሮጳን ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፡ ከያዙ ፡ በኋላ ፡ በዚያው ፡ ተንዘራፍጠው ፡ ተቀመጡ ።

፲፪ ፤ ለጊዜው ፡ ሮማውያን ፡ ተምረውት ፡ የነበረ ፡ የመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፤ የቅኔ ፡ ጥበብ ፤ ቀለም ፡ መቀባት ፤ ደንጊያ ፡ መጥረብና ፡ የሙዚቃ ፡ ትምህርት ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ብለው ፡ በገነኑባቸው ፡ አገሮች ፡ ገና ፡ አልታወቁም ፡ ነበር ።

፲፫ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አዲሶቹ ፡ ባላገሮች ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረሱ ። አሁንም ፡ ዛሬ ፡ በዚያው ፡ ያሉትን ፡ አውራጃዎች ፡ የያዙ ፡ ነገዶች ፡ የነዚያው ፡ የቀድሞቹ ፡ ዘሮች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ይታሰባሉ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ የፈረንሳይን ፡ ታሪክ ፡ እንቀጥላለን ፡

## ጥያቄ ።

፩ ፤ በሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ሰው ፡ የገባበት ፡ እንደምንድነው ፡ ?
ከየነገዱ ፡ በየጐሣው ፡ እየሆነ ፡ የፈለሰውን ፡ ሕዝብ ፡ በምን ፡ እንመስለው ፡ ?

፪ ፤ እነዚህ ፡ ስደተኞች ፡ ሕዝብ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

፫ ፤ ጦርነታቸው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፬ ፡ የነዚህ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ሁኔታ ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ?

፭ ፤ እንደምን ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፮ ፤ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ካሉት ፡ ነገድ ፡ በጣም ፡ የታወቁት ፡ የትኞች ፡ ናቸው ፡ ?

፯ ፤ አናኑዋራቸው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ተናገር ።

፰ ፤ ወደፊት ፡ አሳባቸው ምን ፡ ሊያደርጉ ፡ ኑርዋል ፡ ?

፱ ፤ የሮማውያን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ የተባሉት ፡ ጣልያንን ፡ የመቱት ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
አላሪክና ፡ አቲላ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፲ ፤ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ አዘውትረው ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፲፩ ፤ የሰሜን ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ በየት ፡ ወገን ፡ ኖሩ ፡ ?

፲፪ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ ? ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
የዛሬው የሰሜን ፡ ነገድ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፴ ፡ ኤውሮጳ ።

### [illegible]ለ ፡ ፈረንሳይ ሕዝብ ፡ መጀመሪያ ፡ ስለ ፡ ጎሎች ።

፩ ፤ ፈረንሳይ ፡ የጥንት ፡ ስሙ ፡ ጎል ፡ ይባላል ። ሕዝቡም ፡ ጎሎች ፡ ወይም ፡ ኬልቶች ፡ ይባላሉ ። እነዚህም ፡ ቅድም ፡ ጦረኞች ፡ ሕዝብ ፡ ብዬ ፡ ያመለከትኋችሁ ፡ ናቸው ። ጥንት ፡ ቊጥራቸው ፡ የበዛ ፡ ኀይለኞች ፡ ነበሩ ። ፫፻፺ ፡ ዓመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ብሬኑስ ፡ የተባለውን ፡ መሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሮምን ፡ ወረሩዋትና ፡ ከተማዪቱን ፡ ያዝዋት ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ካሚሉስ ፡ ወዲያው ፡ አባረራቸው ።

፪ ፤ ደግሞ ፣ ሌላ ፣ ብሬንስ ፣ የተባለ ፣ ያዙና ፣ እንደ፣ነገርኋችሁ፣ ግሪክን፣ወረሩ ። በጁሊውስ ፣ ቄሣር ፣ ዘመን፣ጎሎች ፣ በሥልጣኔ ፣ ረገድ ፣ ጥቂት ፣ ከፍ ፣ ብለው፣ ነበሩ ። ነገር ፣ ግን ፣ ከረመኔነት ፣ ሥራቸው ፣ ጥቂት፣አስቀሩ ፣ እንጂ፣ፈጽመው፣ እንደ፣አራዊት ፤ ነበሩ ፣ የሆነ ፣ ሆኖ ፣ መልካሞች ፤ ከተሞችና ፣ በደንጊያ፣የተገ ነቡ ፣ ምሽጎች ፣ ነበሩዋቸው ።

፫ ፤ ቄሣር ፣ ወደ ፣ አገር ፣ ውስጥ ፣ በገባ ፣ ጊዜ ፣ ጎሎች ፣ በጀርመን ፣ ሕዝብ ፣ በጣም ፣ ተጨቁነውና ፣ ተጠቅተው ፣ አገኘ ፤ መጀመርያ ፣ ከነዚህ ፣ ከሚያጠቁዋ ቸው ፣ ጠላቶቻቸው ፣ ጎቶችን ፣ የሚያድን ፣ መስሎ ፣ ታየ ።

፬ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ መምጣቱ ፣ እነርሱን ፣ ሊወጋቸው፣እንደ፣ሆነ ፣ አሳቡን ፣ ሕዝቡ፣ አወቁበትና ፣ ከዚህ ፣ ወዲያ ፣ መከላከል ፣ ጀመሩ ። በሚያስገርም ፣ ብልሀትና ፣ ጀግንነት ፣ ቄሣርንና ፣ ሠራዊቱን ፣ ዘጠኝ ፣ ዓመት ፣ ሙሉ ፣ ተዋጉት ። ነገር፣ግን፣ በጦር ፣ መሣሪያ ፣ ረገድ ፣ ከጎሎች ፣ ይልቅ ፣ ሮማውያን ፣ የተሻለ ፣ የጦር፣ መሣ ሪያ ፣ መሥራት ፣ ይችሉ ፣ ስለ ፣ ነበር ፣ መሣሪያቸው ፣ ተጎሎች ፣ መሣሪያ ፣ የበ ለጠ ፣ ነው ። ወታደሮቻቸውም ፣ የጦር ፣ ሥራ፣ ተምረዋል ።

፭ ፤ በዚያን ፣ ጊዜ ፣ ከነበሩት ፣ ከታላላቆች ፣ መሪዎች ፣ አንዱ ፣ ጁሊውስ ፣ ቄሣር ፣ በሮም ፣ ጭፍሮች ፣ ኀይል ፣ እየተረዳ ፣ ሊገዛቸው ፣ ፈልጎ ፣ ነበር ። ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ ጋር ፣ ጎሎች ፣ አገራቸውን ፣ ለማዳንና ፣ ከጠላት ፣ ለመከላከል ፣ ጀግኖችና ፣ ሞገደ ኞች ፣ ነበሩ ። ስለ፣ሆነ፣የቄሣርን ፣ የጦር ፣ ብልሀት ፣ ሁሉ፣ማወቅ፣ያስፈልግ፣ነበር ።

፮ ፤ ቄሣር ፣ ጎሎችን ፣ ድል ፣ ለማድረግ ፣ ፱ ፣ ዓመት ፣ ተዋግቶ ፣ በዚሁ ፣ ውጊት ፣ አንድ ፣ ሚሊዮን ፣ ሰው ፣ ወድቋል ። ፶፣ ዓመት ፣ ከክርስቶስ፣ልደት፣በፊት፣ቄሣር፣ ድል ፣ ካደረገበት ፣ ቀን ፣ ጀምሮ ፣ ጎል ፣ የሮም ፣ ግዛት ፣ ሆነ ፤ ሕዝቡም ፣ ጥቂት ፣ በጥቂት ፣ እያሉ ፣ የሮማውያንን ፣ ጠባይና ፣ ልማድ ፣ ተማሩ ። ቋንቋቸው ፣ እንኳ፣ ሳይቀር ፣ ተለወጠና ፣ ላቲን ፣ የሚመስለውን ፣ ለመዱ ። ነገር፣ግን ፣ በሦስተኛውና ፣ ባራተኛው ፣ መቶ ፣ ዓመት ፣ ፊት ፣ እንደ፣ተናገርሁት፣ፍራንክስ ፣ የተባሉ ፣ ነገደ ፣ ጀርመን ፣ የሚበልጠውን ፣ የጎልን ፣ ክፍል ፣ እጅ ፣ አደረጉት ።

፯ ፤ መጀመሪያ በጎል ፣ ይኖሩ ፣ የነበሩት ፣ ፍራንኮች ፣ ፋራሞን ፣ የተባለ ፣ መሪ ፣ ነበራቸው ። ይህም ፣ በ፬፻፳፰ ፣ ሞተና ፣ በስፍራው ፣ ክሎዲዎን ፣ የተባለ ፣ ልጁ ፣ ተተካ ። ይህም ፣ እጅግ ፣ ጸጕረ ፣ መልካም ፣ ነበር ። ክሎዴዎን ፣ በ፬፻፵፰ ፣ ሞተ ። በስፍራው ፣ ሜሮቩስ ፣ ተተካ ፤ ሜሮቩስም ፣ በ፬፻፶፰ ፣ ሞተ ። በስፍራው ፣ ቺልዲ ሪክ ፣ ተተካ ፤ ከመጨረሻው ፣ በቀር ፣ ከነዚህ ፣ ነገሥታት ፣ የታወቁት ፣ እጅግ ፣ ጥቂቶች ፣ ናቸው ።

<u>ጥያቄ ።</u>

፩ ፤ የፈረንሳይ ፣ የጥንት ፣ ስሙ ፣ ማን ፣ ይባላል ፣ ? ሕዝቡ ፣ ማን ፣ ይባላሉ ፣ ? ብሬኑስ ፣ ከተባለ ፣ ሰው ፣ በታች ፣ ሁነው ፣ ሕዝቡ ፣ ምን ፣ አደረጉ ፣ ?

፪ ፤ ግሪክን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ወረሩት ፡ ? በጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ እን ዴት ፡ ነበሩ ፡ ? ከተሞቻቸው ፡ እንዴት ፡ ነበሩ ።
፫ ፤ ቄሣር ፡ ወደ ፡ አገር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አገኘ ።
፬ ፤ ሕዝቡ ፡ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ያገኙት ፡ ምንድነው ፡ ? ምን ፡ አደረጉ ? ሮማውያን ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፭ ፤ ጎሎች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ? እነሱን ፡ ለመግዛት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ምን ፡ ነበር ፡ ?
፮ ፤ በጎሎችና ፡ በሮማውያን ፡ ትግል ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?
ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ ጎሎች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ፍራንኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፯ ፤ ፋራሞን ፤ ክሎዴን ፤ ሜሮቪውስ ፤ እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፴፩ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ክሎቢንስና ፡ ስለ ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ፔፒን ።

፩ ፤ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረተ ፡ ቺልድሪክ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ። ልጁ ፡ ክሎቪስ ፡ ተከተለው ፤ ክሎቪስ ፡ ያሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ሮማውያንን ፡ ከፈረንሳይ ፡ አገር ፡ እየነዳ ፡ አስወጣቸው ። ቀጥሎም ፡ በኋላ ፡ ጀርመኖችን ፡ ድል ፡ አደርጓል ።

፪ ፤ ክሎቪስ ፡ ከክርስቲያኒቱ ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተጋባ ፡ ሥራው ፡ የሚከናወንለት ፡ እስዋ ፡ በምታመልከው ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሰበ ። ስለዚህ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነና ፡ በ፬፻፺፮ ፡ ዓ. ም. ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዜጎቹ ፡ ጋር ፡ በበዓለ ፡ ልደት ፡ ተጠመቀ ። ክሎቪስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፈረንሳይ ፡ ባያሎች ፡ ትንንሾች ፡ ነገሥታት ፡ ተከፋፈ ለች ። እነዚህም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተነቋቈሩ ፡ በሕዝቡ ፡ መኻከል ፡ ትልቅ ፡ ሁከት ፡ አስነሡ ። ከነዚህም ፡ ያንደኛው ፡ ሚስት ፡ ዐሥር ፡ ነገሥታት ፤ ወይም ፡ የነገሥታትን ፡ ልጅ ፡ ገድላለች ፡ ተብላ ፡ ተከሳ ፡ ነበረች ።

፫ ፤ ትንሹ ፤ ወይም ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ፔፒን ፡ እነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ እየገ ፈተረ ፡ አስወጥቶ ፡ እርሱው ፡ ራሱ ፡ ዋና ፡ የፈረንሳይ ፡ ገዢ ፡ ሆነ ። ሰውነቱ ፡ እጅግ ፡ ትንሽ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ቁመቱ ፡ አራት ፡ ፊት ፡ ተኩል ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚች ፡ ትንሽ ፡ ሰውነት ፡ ውስጥ ፡ ኀይለኛ ፡ መንፈስ ፡ ነበረበት ።

፬ ፤ እንዲህ ፡ ሲሆን ፡ ከልክ ፡ ያለፈ ፡ ኀይልና ፡ ጒልበት ፡ ነበረው ፤ ስለርሱ ፡ እን ዲህ ፡ ይተረክለታል ። በሰውነቱ ፡ ማነስ ፡ ከማለሟሎቹ ፡ ወገን ፡ እንደሚሥቁበት ፡ ዐውቆ ፡ ባንድ ፡ ታላቅ ፡ ኀይለኛና ፡ ጒልበታም ፡ በሚባል ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ኀይል ፡ በሱም ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ ለማሳየት ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረገ ። ስለዚህ ፡ አንበሳና ፡ ኰርማ ፡ ሲዋጉ ፡ እንድታዩ ፡ ብሎ ፡ መኳንንቱን ፡ ሁሉ ፡ ጠራቸው ።

፭ ፤ አንበሳው ፡ በሚያስፈራ ፡ አኳኋን ፡ ሆኖ ፡ አገሣና ፡ ወዲያው ፡ ዘሎ ፡ በኰርማው ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጣበቀ ፡ ሥጋውን ፡ በጥፍሩ ፡ ሰቅስቆ ፡ ያዘው ። ኰርማውም ፡ ከሕ መሙ ፡ የተነሣ ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡ አገሣ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡

ፔፒን ፡ የቻለውን ፡ ያህል ፡ ቁመት ፡ ለማግኘት ፡ ተነሥቶ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ እንደ ሆነ ፡ በጥፍሩ ፡ ቆመ ። አንበሳውና ፡ ኮርማው ፡ ባገሡት ፡ መጠን ፡ እንዲሁም ፡ ንጉሡ ፡ በዙሪያው ፡ ለነበሩት ፡ ሁሉ ፡ ድምፁን ፡ አሰምቶ ፡ ጮኸ ።

፮ ፤ ሕዝቡንም ፡ «ማነው ፡ ከላንት ፡ አንበሳውን ፡ የሚያስለቅቀው ፡» ቢላቸው ፡ ሕዝቡም ፡ ያንበሳውን ፡ ጥፍር ፡ ቀርበው ፡ ተኮርማው ፡ ለማስለቀቅ ፡ አሳብ ፡ አልነበራቸውምና ፡ ሁሉም ፡ አፍረው ፡ ቆሙ ። ጀግናው ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ፔፒን ፡ «እንግዲያስ ፡ እኔው ፡ ራሴ ፡ አስለቅቀዋለሁ ፡» አለና ፡ ከዙፋኑ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ዱብ ፡ ብሎ ፡ በርዝመት ፡ እርሱን ፡ የሚያህለውን ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘና ፡ እያወዛወዘ ፡ ኮርማውን ፡ በጥፍሩ ፡ ሰቅስቆ ፡ ወደያዘው ፡ አንበሳ ፡ ቀረበ ።

፯ ፤ አንበሳውም ፡ ይህን ፡ የሚያስፈራ ፡ ትንሽ ፡ አሸናፊ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የሚያስፈራ ፡ መንጋጋውን ፡ ለማሳየት ፡ አፉን ፡ ከፈተና ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ቀርበ ፡ ያፉ ፡ ጕርሻ ፡ ሊያደርገው ፡ አሰበ ። ነገር ፡ ግን ፡ ትንሹ ፡ ንጉሥ ፡ ፔፒን ፡ ሰይፉን ፡ በነዘረ ፡ ጊዜ ፡ በትክክል ፡ አንገቱን ፡ ስለ ፡ አገኘው ፡ ያንበሳው ፡ ራስ ፡ በኮርማው ፡ ጐን ፡ ወደቀና ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የቀረው ፡ አካሉ ፡ ወደቀ ። ከዚያን ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ሕዝቡ ፡ ባጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ በፔፒን ፡ ከመሣቅ ፡ ይልቅ ፡ የሚያገሣውን ፡ አንበሳ ፡ ጋማ ፡ መያዝ ፡ የቀለለ ፡ ሆኖ ፡ አገኙት ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ቺልዲሪክ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ? ክሎቪስ ፡ ማነው ፡ ?

፪ ፤ ክሎቪስ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመሆን ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ ያደረገው ፡ ስለ ምንድን ፡ ነው ፡ ?

ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጠመቀ ፡ ? እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፈረንሳይ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ነገሥታቱ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

፫—፬ ፤ ስለ ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ፔፒን ፡ ተናገር ። ሕዝቡን ፡ ምን ፡ ለማሳየት ፡ ጠራቸው ፡ ?

፭ ፮—፯ ፤ ንጉሡ ፡ ፔፒን ፡ ካንበሳ ፡ ጋር ፡ ውጊያ ፡ እንደ ፡ ገጠመ ፡ ተናገር ።

፰ ፤ ጀግንነቱ ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ተሰማቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፴፪ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ሻርለማኝ ፡ መንግሥ ።

፩ ፤ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ፔፒን ፡ ሻርለማኝ ፡ ወይም ፡ ታላቁ ፡ ሻርልስ ፡ የተባለ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ፤ ይህም ፡ ኀይለኛና ፡ አሸናፊ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ቁመቱ ፡ ከሰባት ፡ ፊት ፡ አንዲት ፡ ኢንች ፡ እንኳ ፡ ያልጐደለው ፡ ነበርና ፡ ስለ ፡ ቁመቱ ፡ ርዝመት ፡ የማዕርግ ፡ ስም ፡ የሚገባው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ተሰጥቶት ፡ ነበር ።

፱ ፤ ሻርለማኝ ፡ የበግ ፡ ለምድ ፡ ይለብስ ፡ ነበር ። መቸውንም ፡ መኳንንቱ ፡ የከበረ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አውሬ ፡ ለማደን ፡ እንዲሄዱ ፡ ይጠራቸው ፡ ነበር ፤ የሚከተሉት ፡ ሁሉ ፡ ልብሳቸው ፡ በጋሬጣ ፡ እንዲቀደድ ፡ ብሎ ፡ በሾኽና ፡ በደን ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ እርሱ ፡ መሪ ፡ ሆኖ ፡ ይወስዳቸው ፡ ነበር ።

፲ ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ አዘውትሮ ፡ ጦርነት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ። ሳክሶን ፡ የሚባሉትንና ፡ ሌሎችንም ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ የሚኖሩትን ፡ ነገድ ፡ አስገብሮአቸዋል ። እንደዚሁም ፡ እስጳንያንና ፡ ጣልያንን ፡ ድል ፡ አድርጎአል ። ወዲያው ፡ የፈረንሳይንና ፡ የጀርመንን ፡ የሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ደባልቆ ፡ ገዝቶአል ። ከዚህ ፡ በላይም ፡ የምዕራብ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መባልን ፡ ተመኝቶ ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ እንዲሁም ፡ ሻርለማኝ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሄዶና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ምእመን ፡ በመሆኑ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታላቁ ፡ መሠዊያ ፡ ጸሎት ፡ እንደማድረግ ፡ ተንበረከከ ። በዚያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ተንበርክኮ ፡ ሲጸልይ ፡ ሳለ ፡ ጳጳሱ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ተወደ ፡ ኋላው ፡ እያመለገ ፡ መጣና ፡ የንጉሥ ፡ ዘውድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አደረገለት ።

፲፪ ፤ ይህም ፡ ያለፉት ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ የሚጭኑት ፡ ዘውድ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በሻርለማኝ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ዘውድ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ «ንጉሥ ፡ በሕይወት ፧ ይኑር ፡» እያሉ ፡ እልል ፡ አሉ ። ሻርለማኝ ፡ ተቈጥቶ ፡ እየተደነቀ ፡ ተግደረደረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ዘውዱን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ጠበቀ ።

፲፫ ፡ በ፰፻፲፬ ፡ ሻርለማኝ ፡ ዕድሜ ፡ ጠግቦ ፡ አርጅቶ ፡ ሞተ ። ሬት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁት ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ የበግ ፡ አጐዛ ፡ እንደ ፡ ካባ ፡ አድርጎ ፡ ይለብስ ፡ ነበር ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አሽከሮቹ ፡ ለነገሥታት ፡ ብቻ ፡ የሚገባውን ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ።

፲፬ ፤ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ ዙፋን ፡ ዘረጉና ፡ ጽሕሙ ፡ ግራጫ ፡ የሆነ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሬሳ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ አኖሩ ። በወገቡ ፡ ሰይፍ ፡ ታጥቋል ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ ዘውድ ፡ ደፍቶአል ፤ ከእግሩ ፡ ሥር ፡ የወርቅ ፡ በትረ ፡ መንግሥትና ፡ ጋሻ ፡ አለ ። በእጁ ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ይዞአል ፤ ቅዱስ ፡ መጽሐፍም ፡ በጕልበቱ ፡ ላይ ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ የሚታይ ፡ የተቀሠተ ፤ ድል ፡ የመንሣት ፡ ምልክትና ፡ የታላቁ ፡ የሻርለማኝ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረበት ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ጌጥና ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ለማይሰማና ፡ ለማይለማ ፡ ሬሳ ፡ ካጠፉ ፡ በኋላ ፡ አሽከሮቹ ፡ መቃብሩን ፡ ዘግተው ፡ ወደ ፡ ሻርለማኝ ፡ ወራሽ ፡ እጅ ፡ ለመንሣት ፡ ሄዱ ።

፲፮ ፤ ይህም ፡ ልጁ ፡ ሉዊስ ፡ ገራሙ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ይህም ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ከሠራው ፡ ሥራ ፡ አንደኛው ፡ የማረከውን ፡ ንጉሥ ፡ ዐይኑን ፡ አስወልቆት ፡ ነበርና ፡ እኔ ፡ ገራም ፡ መባሉን ፡ አላውቅም ። ሉዊስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱን ፡ ለሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ተወላቸው ። ወዲያው ፡ ያንጊዜውን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ መዋጋት ፡ ጀመሩ ። ባንዱ ፡ ውጊታቸው ፡ ብቻ ፡ ከጦርነቱ ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ በሰይፍ ፡ አፍ ፡ ወደቀ ፡ ይባላል ።

፲ ፤ ከፈረንሳይ ፡ ነገሥታት ፡ የተከናወኑላቸው ፡ ክርልስ ፡ ራሰ ፡ በራው ፤ ሉዊስ፡ ድዳው ፤ ክርል ፤ ወፍራሙ ፤ ክርል ፡ የዋሁ ፤ ሉዊስ ፡ እንግዳውና ፡ ሁግኬፕት ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ በመጽሐፌ ፡ ሊጻፍ፡ የሚያስፈልግ፡ ሥራ፡ አልሠሩም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሻርለማኝ፡ማነው ፡ ? አለባበሱ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የሕዝቡ ፡ ልብስ ፡ እን ዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፪—፫ ፤ ሻርለማኝ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ? በየት ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፡ ?

፬ ፤ ምን ፡ ተመኘ ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ? የዘውዱን ፡ በዓል ፡ ሁኔታ ፡ ተናገር ።

፮ ፤ ሻርለማኝ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ? ሬሳውን ፡ ምን ፡ አለበሱት ፡ ?

፳ ፤ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ምን ፡ አቆሙ ፡ ?

፱ ፤ ሉዊስ ፡ ገራሙ ፡ የተባለ ፡ ማነው ፡ ? ስለርሱ ፡ ምን ፡ ተባለ ፡ ? ሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፤ ?

፲ ፤ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ የወረሱ ፡ ነገሥታት ፡ እነማናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፴፫ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ መስቀል ፡ ጦርነት ።

፩ ፤ በቱርክ ፡ እጅ ፡ የነበረችውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለማዳን ፡ የኤውሮጳ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ፡ጀመሩት፡ቅዱስ ፡ ጦርነት ፡ ጥቂት ፡ አሳብ ፡ እሰጣችኋለሁ ። ይህችን ፡ ከተማ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ክርስቶስ ፡ በዚህች፡ ስፍራ፡ አስተማረ ፤ ብዙ ፡ ተአምራትም፡ አሳየ ፤ በዚህችው ፡ ስፍራ ፡ ተቀበረና ፡ በድኑ ፡ ዐረፈ ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ያከብ ሩዋታል ።

፪ ፤ ቅድስት ፡ ከተማ ፡ እያሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ የሚያከብሩዋት፡ ስለ፡ሆኑ፡ልዩ ፡ ልዩ፡የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ የተባሉ ፡ ሁሉ ፡ ይህችን ፡ ቅድስት፡ ከተማ ፡ ለመጐብኘት ፡ በእግር ፡ የማይሄዱ ፡ የሉም ። ኃጢአት ፡ ለሠሩት ፡ ሰዎች ፡ ወደዚች ፡ ቅድስት ፡ ኢየሩሳሌም፡የሄዳችሁ፡እንደ፡ሆነ ፡ የኃጢአት ፡ ሥር የት ፡ ታገኛላችሁ ፤ እያሉ ፡ የካቶሊክ ፡ ቀሳውስት ፡ እንዲህ ፡ የመሰለውን፡ትእዛዝ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ መጫናቸው ፡ የተለመደ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ብቻ ፡ የኃጢአት ፡ ሥር የት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ።

፫ ፤ መቸውንም ፡ ቢሆን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚሄዱ ፡ ክርስቲያናት፡መከራንና ፡ ግፍን ፤ ውርደትን ፡ ከቱርክ ፡ እንደ፡ተቀበሉ፡ናቸው ። ይህም ፡ መደረጉ፡ኢየሩሳሌ ምንና ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉትን፡አውራጃዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚገዛ ፡ ቱርክ፡ስለ፡ነበረ፡ነው ። ክርስቲያኖችም ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ተመልሰው ፡ ቱርክ ፡ ያደረገባቸውን ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ አወሩ ። ይህም ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ሁሉ ፡ ባስቄጣ ፡ ጊዜ ፡ ቅድስት፡ አገርን ፡ ከቱርክ ፡ እጅ ፡ ለመንጠቅ ፡ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ ተሰብስበው ፡ አንድነት፡ ለማድረግ ፡ አሰቡ

፬ ፤ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የሮሙ ፡ ጳጳስ ፡ ትልቅ ፡ ኀይል፡ነበረው ፤ አብልጦም፡ኀይል ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ ፤ ይህም ፡ አሳብ ፡ ተፈጽሞ ፡ አገሩ ፡ የተያዘ፡እንደ፡ሆነ ፡ በጳለስቲና ፡ ላይ ፡ ሥልጣኑን ፡ ለማስፋፋት ፡ ይችላል ።

፭ ፤ ለመጀመሪያው ፡ ጦርነት ፡ ዋና ፡ ሆኖ ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ ያነሣሣው፡ጴጥሮስ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ ነው ። ይህም ፡ በችጋር ፡ ጕኑ ፡ የተጣጋ ፡ መነኰሴ ፡ ነበር ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ ቆብ ፡ ሳያደርግ ፡ ወገቡን ፡ በገመድ፡ታጥቆ ፤ ሻካራ፡ልብስ፡ ለብሶ ፡ ይዞር ፡ ነበር ፤ ሰውዬው ፡ አጭር ፡ ነው ። ክንዱና ፡ እግሩ ፡ ራቁቱን፡ ሆኖ ፡ ለሰውነቱ ፡ መሸፈኛ ፡ ብቻ ፡ ለብሷል ።

፮ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ውን ፡ ማስፈራሪያ ፡ የመሰለውን ፡ ነገር ፡ ከማክበር ፡ ይልቅ ፡ ሣቅ ፡ የሚያስነሣ ፡ ሆነ ። ጴጥሮስ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጳለስቲና ፡ ነበረና ፡ የቱርክን ፡ ስድብ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ ያየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ፡ስለ፡ተናገረ ፡ ሕዝቡም ፡ የሚናገረውን ፡ እየሰሙ ፡ በጣም ፡ አዘኑ ።

፯ ፤ ጴጥሮስ ፡ ካንዱ ፡ ከተማ ፡ ወደሌላው ፡ ይዞር ፡ ነበር ፤ በሚሄድበት ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ የሚናገረውን ፡ ለመስማት ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ይሰበሰብ ፡ ነበር ። ወዲያው፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ተነሣሣና ፡ ነገሥታት ፡ ባንድነት ፡ ሁነው ፡ ቱርክን ፡ ለመ ውጋት ፡ ጦራቸውን ፡ ሰበሰቡ ። በሺ፺፮ ዓ. ም. ሁለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰው፡በጴ ጥሮስ ፡ እግር ፡ ሆኖ ፡ ወጣ ፤ እርሱ ፡ ከባድ ፡ የሆነ ፡ መስቀሉን ፡ በትከሻው፡ተሸ ከመ ፤ የተከተሉትም ፡ በልብሳቸው ፡ ላይ ፡ የቀይ ፡ ልብስ ፡ መስቀል ፡ ሰፉ ።

፰ ፤ ይህ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ገና ፡ ወደ ፡ እስያ ፡ ሳይደርስ ፡ ሡልጣን ፡ ሶሊማን፡ ገጠማቸውና ፡ ክፉኛ ፡ ስለተዋጋቸው ፡ ድል ፡ ሆኑ ። ድል ፡ ለማድረጉ ፡ መታሰ ቢያ ፡ ብሎ ፡ ዐጽማቸውን ፡ እንደ ፡ ፒራሚድ ፡ አድርጎ፡ ከመረው ። ሁለተኛም፡ ገጥመው ፡ ቢዋጉ ፡ እንደዚሁ ፡ ሆነ ።

፱ ፤ በፊተኛው ፡ ውጊት ፡ ፷፻፵—ሺ፡ክርስቲያኖች፡ሕይወታቸውን፡ አጡ ። ይህም፡ ሁሉ ፡ መታረድ ፡ የተደረገው ፡ ገና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ባይናቸው፡ ሳያይዋት፡ነው ።

፲ ፤ የፊተኛው ፡ የመስቀል ፡ ጦር ፡ ክፍል ፡ የሚሆን፡ሌላ፡ጭፍራ፡ነበር ፤ ይህም ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ ተዋግቶ ፡ ተከናወነለት ። ይኸውም፡፹ሺ፡ይሆናል፡ይህም ፡ ጎድፍሬ ፡ በተባለ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ገዢ ፡ ተመርቶ ፡ የወጣ ፡ ነበር ፤ በትንሽ፡ እስያ ፡ በኩል ፡ መኻል፡ለመኻል፡ገብቶ፡የቱርክን፡አያሎች፡ከተሞች፡ያዘ ። ቀጥሎ፡ በሺ፺፱ ዓ. ም. ኢየሩሳሌምን ፡ ማረከ ፤ ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሺ፩፻፹፯ ፡ ቅድ ስት ፡ አገር ፡ በክርስቲያኖች ፡ እጅ ፡ ተጠብቃ ፡ ቈየች ። እንደ ፡ ገና፡ቱርክ፡መልሶ ፡ በማረካት ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ በርሱው ፡ እጅ ፡ ነበረች ።

፲፩ ፤ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ካምስት ፡ ጊዜ፡አያንስም ፤ የኋለኛው፡ከሺ፡፩፻፵፯፡ዓ. ም. ጀምሮ ፡ ሌሎቹም ፡ ሁሉ ፡ አልተከናወነላቸውም ። በዚህ ፡ ጦርነት፡ያለቁት፡ ከሁ ለት ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ አያንሱም ።

፲፪ ፤ በዚሁ ፡ በመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ መልካም ፡ ሰዎች ፤ እንደ ፡ ነበሩበት ፡ ይታያል ። ብልሆችም ፡ ከውስጡ ፡ አይጠፉም ፤ ከመሪዎቹ ፡ ውስጥ ፡ አያሎች ፡ ጀግኖች ፡ ነበሩበት ፤ የብረት ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፤ ፈረስ ፡ እየተቀመጡ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ። ከጦሩ ፡ የሚበዛው ፡ ክፍል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ነበር ። እኩሌቶችም ፡ የሃይማኖት ፡ ቅናት ፡ የመላባቸው ፡ ደካሞች ፡ ነበሩ ፤ የሚበዙትም ፡ ከተማ ፡ ሲሰበር ፡ ለመዝረፍና ፡ ለመቀማት ፡ ብለው ፡ ዘመቻውን ፡ ተከትለው ፡ የመጡ ፡ ሌቦችና ፡ ቀማኞች ፡ ናቸው ።

፲፫ ፤ ግን ፡ በመስቀል ፡ ጦርነት ፡ የብዙዎች ፡ አሳብ ፡ ጥቅምን ፡ መፈለግ ፡ ነበር ፤ በነዚህ ፡ ዘመቻዎች ፡ ምንም ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ቢፈስ ፡ የኤውሮጳ ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ የሚያደርስ ፡ ብዙ ፡ ብልሀትና ፡ ጥበብ ፡ ከምሥራቅ ፡ አምጥተዋል ። በዚህና ፡ በሌላም ፡ መንገድ ፡ አድርጎ ፡ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ታላቅ ፡ ጠቀሜታ ፡ አስገኝቶአል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ክሩሴድ ፡ የተባሉ ፡ ምንድናቸው ፡ ? ይህን ፡ ሥራ ፡ ለምን ፡ ጀመሩ ፡ ?
ስለምን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያከብራሉ ፡ ?

፪ ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለምን ፡ ይሄዳሉ ፡ ?

፫ ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሄዱትን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ቱርኮች ፡ እንዴት ፡ ያደርጉዋቸው ፡ ነበር ፡ ?
ምን ፡ አደረጉዋቸው ፡ ? ወደዚያ ፡ መሄዳቸውስ ፡ ለምንድነው ፡ ?

፬—፭ ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
ጴጥሮስ ፡ ስለተባለው ፡ ባሕታዊ ፡ መነኵሴ ፡ ተናገር ።

፮ ፤ ጴጥሮስ ፡ ባሕታዊው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ?

፯ ፤ በስብከቱ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? በ፲፻፺፭ ፡ ዓ. ም. ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

፰ ፤ በእስያ ፡ ጦርነት ፡ ጀማሪው ፡ ጭፍራ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ? ሡልጣን ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፱ ፤ የመጀመሪያው ፡ የመስቀል ፡ ጦር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? የቱን ፡ ከተማ ፡ ያዘ ፡ ?

፲ ፤ ጎድፍሬ ፡ በተባለ ፡ ሹም ፡ ተመርቶ ፡ የወጣው ፡ ጦር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የቱን ፡ ከተማ ፡ ያዘ ፡ ?
ቱርክ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የያዘ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ?

፲፩ ፤ በዚያ ፡ የነበሩ ፡ የመስቀል ፡ ጦር ፡ ወታደሮች ፡ ስንት ፡ ነበሩ ፡ ?
ፊት ፡ የመስቀል ፡ ጦር ፡ የተጀመረው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ?
የመጨረሻው ፡ የት ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡ ? በመስቀል ፡ ጦር ፡ ጊዜ ፡ ሕይወታቸውን ፡ ያሳለፉ ፡ ሰዎች ፡ ስንት ፡ ናቸው ፡ ?

፲፪ ፤ ስለ ፡ መስቀል ፡ ጦርነት ፡ ምን ፡ ተገለጸ ፡ ? የጦር ፡ መሮች ፡ የነበ
ሩት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ?
የጠፉ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲፫ ፤ የመስቀል ፡ ጦር ፡ ምን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አደረገ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፴፬ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ጥንታዊ ፡ አገዛዝ ፡ ዐይነት ።

፩ ፤ የፈረንሳይን ፡ ታሪክ ፡ ለመግለጽ ፡ አሁን ፡ ጊዜው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የምታስቡ ፡ ይመስለኛል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ አትቈጡ ፡ ስለ ፡ ነገሥታትና ፡ ስለ ፡ ታላቅ ፡ ጦርነታቸው ፡ ብቻ ፡ አድርጎ ፡ የሰውን ፡ ታሪክ ፡ መተረክ ፡ ለማንም ፡ አይገባውም ። ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ እንደሚኖሩ ፤ ገዦቻቸውም ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ይገዙዋቸው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ማሰባችንን ፡ ልንረሳው ፡ አይገባም ።

፪ ፤ ስለ ፡ አጭሩ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ፔፒንና ፡ ስለ ፡ ሻርለማኝ ፡ ስለ ፡ ጳጳሱም ፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ ገዦች ፡ ምን ፡ እንዳደረጉ ፡ ብናገር ፡ ዜጎቻቸው ፡ ደግሞ ፡ ያደረጉትን ፡ አታውቁም ። በደስታ ፤ ወይም ፡ በኀዘን ፤ በጌትነት ፡ ወይስ ፡ በድኀነት ፡ በነጻነት ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፤ ወይም ፡ በክፉ ፡ አገዛዝ ፡ በመከራ ፡ መኖራቸውን ፡ አታውቁም ።

፫ ፤ ስለ ፡ ጥንት ፡ አገዛዝና ፡ ቺባልሪ ፡ ስለሚባሉ ፡ አለቆች ፡ ልታስተውሉዋቸው ፡ የሚገቡ ፡ ጥቂት ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮች ፡ ብናገር ፡ ይቅርታ ፡ እንድታደርጉልኝ ፡ አምናለሁ ። የሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ባላገሮች ፡ መዋጋትና ፡ የማያሳርፍ ፡ የመዘር ፡ ጠባይ ፡ እንዳለባቸው ፡ ነግሬያችኋለሁ ። ጦርነት ፡ ለሰዎች ፡ በውነት ፡ ዋና ፡ ሥራቸው ፡ ነው ። ከነርሱም ፡ ጥቂቶቹ ፡ በእርሻ ፡ ላይ ፡ ይኖራሉ ። የሚበዙት ፡ በወታደርነት ፡ ይኖራሉ ። ማለት ፡ ጭራሽ ፡ በወታደርነት ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ። ወይም ፡ ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ወታደርነት ፡ የሚገቡ ፡ ማለቴ ፡ ነው ።

፬ ፤ ጥቂቶች ፡ ቤት ፡ በመሥራት ፡ በጦር ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ ሌላም ፡ ለሕዝብ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ በመሥራት ፡ ይኖራሉ ። እንደዚህ ፡ የመሰሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚያስፈልግ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለጦርነት ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ መሄድ ፡ አለባቸው ።

፭ ፤ ፊት ፡ እንደተናገርሁት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሰዎች ፡ ዋናው ፡ ሥራቸው ፡ ጦርነት ፡ ብቻ ፡ ነበር ፤ ሌሎቹ ፡ ነገዶች ፡ ሲመጡባቸው ፡ መመከት ፤ ወይም ፡ በሌሎች ፡ ነገዶች ፡ ላይ ፡ ዘምተው ፡ ድል ፡ ማግኘት ፡ ነበር ። አለቆቻቸው ፤ ወይም ፡ ገዦቻቸው ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ የሚጣጣሩና ፡ ብርታት ፡ ያላቸው ፡ ጀግኖች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

፮ ፤ አንድ ፡ አገር ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ ከተሸነፈ ፡ በኋላ ፡ መሬቱም ፡ ከተማውም ፤ መንደሩ ፤ ወርቁም ፤ ብሩም ፤ ንግዱም ፤ ፈረሱና ፡ እንስሳው ፡ ሁሉ ፤ ማንኛውም ፡

ነገር ፡ የተሸነፈው ፡ ገንዘብ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፤ የድል ፡ አድራጊው ፡ ምርኮ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ። ድል ፡ የሆኑትም ፡ ወገኖች ፡ ይገደላሉ ፤ ወይም ፡ ይማረካሉ ። አለዚያም ፡ በባርነት ፡ ይገዛሉ ።

፮ ፤ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ያስደንቃል ። ዘመቻ ፡ ዘምቶ ፡ በጦርነት ፡ የሌላውን ፡ ሕዝብ ፡ መሬትና ፡ ገንዘብ ፡ መዝረፍ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይታሰብም ። ነገር ፡ ግን ፡ ለተመለከተው ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ጨዋታ ፡ ይቈጠራል ። ወታደሮች ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ መከራና ፡ ሥቃይ ፡ እንደሚያገኛቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ብዙዎች ፡ ቈስለው ፡ አካላቸውን ፡ ያጐድላሉ ። እኩሉም ፡ ሙተው ፡ ይቀራሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ ካለቀ ፡ በኋላ ፡ ከሞት ፡ የተረፉት ፡ የአራዊትን ፡ ሕዝብ ፡ ልማድ ፡ ተከትለው ፡ ድል ፡ ያደረጉበትን ፡ ቀን ፡ አክብረው ፡ በዓል ፡ ያደርጋሉ ። ይጠጣሉ ፡ ይዘፍናሉ ፤ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ጨዋታ ፡ ያደርጋሉ ።

፯ ፤ በጦርነቱ ፡ መኻከል ፡ የተደረገውን ፡ ውጊት ፡ አስመስለው ፡ ያሳያሉ ። ወይም ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ መርጠው ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ በሰይፍ ፡ እንደሚዋጉ ፡ አስመስለው ፡ ያሳያሉ ፤ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የሠሩትን ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ያዩትንም ፡ የሰሙትንም ፡ ወይም ፡ የደም ፡ ማፍሰስና ፡ የውጊያ ፡ ዘፈን ፡ በመዝፈን ፡ በዓላቸውን ፡ ያስረዝማሉ ።

፰ ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለመዝፈን ፤ ወይም ፡ ታሪክ ፡ ለመናገር ፡ ስጦታ ፡ አለው ። እንዲህ ፡ የመሰለውም ፡ ሰው ፡ በተሰጠው ፡ ስጦታ ፡ እንዲያጫውት ፡ ይጠራል ። እርሱም ፡ ንጉሥ ፤ ወይም ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ካንበሳና ፡ ከሌላም ፡ አውሬ ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ለሕዝቡ ፡ እየተረከ ፡ ያጫውታቸዋል ።

፱ ፤ ወይም ፡ የሚያስደንቅ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሠሩት ፡ አለቆች ፡ ይናገራል ። ወይም ፡ አንድ ፡ ታሪክ ፡ ከራሱ ፡ ይፈጥርና ፡ በጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ ሩቅ ፡ ስለሚሄዱ ፡ መናፍስት ፡ ይናገራል ። ወይም ፡ ስለ ፡ ተገደሉ ፡ ገገሮች ፡ ነፍሳቸው ፡ ቀድሞ ፡ ወደምትኖርበት ፡ ስፍራ ፡ በሌሊት ፡ እንደምትመጣ ፡ ይናገራል ።

፲ ፤ እነዚህን ፡ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ጦር ፡ ድካማቸው ፡ የሚከፍላቸው ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጨዋታ ፡ ነበር ። ቢሆንም ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ። በነዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ጦርነት ፡ የንግድን ፡ ስፍራ ፡ ወስዶታል ። የጦርነት ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ የሌላውን ፡ ሕዝብ ፡ መሬትና ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ ነው ። በጭፍ ፡ የዘረፉ ፡ ዐቅድ ፡ ማለት ፡ አያሎች ፡ ነገዶች ፡ ብዙ ፡ የቀማኞች ፡ እጆች ፡ ብለው ፡ ያምኑ ፡ ይሆናል ።

፲፩ ፤ አንድ ፡ አገር ፡ ተዋግቶ ፡ ድል ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ድል ፡ አድራጎቹ ፡ እንደ ፡ ማዕርጋቸው ፡ መጠን ፡ የምርኮውን ፡ ገንዘብ ፡ ይከፋፈሉታል ። የሚበልጠውን ፡ ክፍል ፡ ንጉሡ ፤ ወይም ፡ አለቃው ፡ ይወስዳል ። ትንሾችም ፡ አለቆች ፡ የሚገባቸውን ፡ ትንሽ ፡ ክፍል ፡ ይወስዳሉ ። ተራ ፡ ወታደርም ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ያነሰ ፡ ክፍል ፡ ያገኛል ። መሬቱንም ፡ የሚከፋፈሉት ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መሬት ፡ ያገኙት ፡ ሰዎች ፡ አለቃቸው ፡ ዘመቻ ፡ በዘዛቸው ፡ ጊዜ ፡ መዝመት ፡ አለባቸው ።

፲፫ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የመሬት ፡ ነገር ፡ አደያዝ ፡ ዛሬ ፡ በዘመናችን ፡ እንደምና ደርገው ፡ አይደለም ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ ራሱ ፡ መሬት ፡ ኖሮት ፡ ቤት ፡ ሊሠራበትና ፡ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ ሊያርሰው ፡ አይችልም ። ከመሬቱ ፡ መል ካሙና ፡ ታላቁ ፡ ክፍል ፡ የንጉሥ ፡ ነው ፤ ዝቅተኛው ፡ ክፍል ፡ የትንንሾች ፡ የመኳንንትና ፡ ያለቆች ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ንጉሡ ፡ ወይም ፡ አንዱ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ከገዛ ፡ መሬቱ ፡ ላይ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጊያ ፡ ያደርግና ፡ ዙሪያውን ፡ እየመሸገ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ይሠራል ። ጢሰ ኞቹ ፡ ወይም ፡ ባሮቹ ፡ የሆኑት ፡ ትንሽ ፡ ጐጆ ፡ እየሠሩ ፡ ዙሪያውን ፡ ይሰፍራሉ ። እነዚህም ፡ ምድር ፡ እያረሱ ፡ ከመሬቱ ፡ ያገኙትን ፡ ፍሬ ፡ ለመኖሪያቸው ፡ የሚበ ቃቸውን ፡ አስቀርተው ፡ የቀረውን ፡ ላለቃቸው ፡ ለመሬቱ ፡ ጌታ ፡ ይሰጣሉ ።

፲፭ ፤ የጥንት ፡ የፊውዳል ፡ አኑዋኑዋር ፡ ሕግ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። በገረ ፡ ገዢ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ጢሰኞች ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ዘመቻ ፡ በዘዛቻው ፡ ጊዜ ፡ የወታደር ነት ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ ግዴታ ፡ አለባቸው ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ ለጦር ነት ፡ ክተት ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ዜጋውን ፡ ሁሉ ፡ ይዞ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ መገኘት ፡ አለበት ።

፲፮ ፤ አገረ ፡ ገዢ ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ በጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ዜጋውን ፡ መጠበቅ ፡ አለ በት ፤ ያገረ ፡ ገዢው ፡ ምሽግና ፡ አዳራሽ ፡ ጠንካራና ፡ የሚበቃ ፡ የሆን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጠላት ፡ በተቃረበ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ወደዚያ ፡ ይገባሉ ።

፲፯ ፤ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ እንደሚቻላቸው ፡ ከጠላት ፡ ይከላከላሉ ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወር ፡ ያህል ፡ ይከበባሉ ፤ ወይናቸውና ፡ ሥንቃቸው ፡ ያለቀባቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ ታሪካቸውን ፡ ይተርካሉ ፡ ዘፈናቸውን ፡ ይዘፍናሉ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ሊረሳ ፡ የማይገባ ፡ ምንድነው ፡ ?
፪ ፤ የሕዝብን ፡ ታሪክ ፡ ቸለል ፡ ብሎ ፡ ለማለፍ ፡ አለመገባቱ ፡ ስለ ፡ ምንድነው ፡ ?
፫ ፤ የሰሜን ፡ ኤውሮጳ ፡ ነገድ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
ሕዝቡ ፡ ምን ፡ ይወዱ ፡ ነበር ፡ ?
፭ ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ሥራችን ፡ ብለው ፡ የያዙት ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?
አለቆች ፡ የተባሉ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ?
፮ ፤ ድል ፡ የሆነው ፡ አገር ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ነበር ፡ ? ሕዝቡሳ ፡ ?
፯ ፤ ጦርነትንና ፡ ዘረፋን ፡ ልናስበው ፡ ይገባናልን ፡ ? ወታደሮችንሳ ፡ ?
፰ ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጦርነት ፡ መኻከል ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፡ ?
፱ ፤ ታሪክ ፡ ነጋሪ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲ ፤ የጥንት ፡ ሰዎች ፡ ጦርነት ፡ የሚያነሡበት ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ?

ጦርነት ፡ ሲባል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ነገዶች ፡ ምን ፡ ይሉት ፡ ይሆን ፡ ?
፲፪ ፤ የምርኮውና ፡ የዘረፋው ፡ አከፋፈል ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? መሬቱስ ፡ ?
፲፫ ፤ በዚሁ ፡ ዘመን ፡ መሬት ፡ እንደምን ፤ ይያዝ ፡ ነበር ፡ ?
፲፬ ፤ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ባሮን ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፡ ?
ሕዝብና ፡ ባለመሬት ፡ እንደምን ፡ ነበሩ ፡ ?
፲፭ ፤ የጢሰኞችና ፡ የተጋገሮች ፡ አስተዳደር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ባለርስቶችና ፡ መልከኞች ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ምንድነው ፡ ?
፲፮ ፤ የመሬቱ ፡ ጌታ ፡ ሊያደርገው ፡ የሚገባው ፡ ምንድነው ፡ ?
፲፯ ፤ ምሽጋቸው ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፴፭ ፡ ኤውሮጳ ።

### ናይት ፡ እየተባሉ ፡ ስለሚሾሙ ፡ ሰዎች ።

፩ ፤ ቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በፈረንሳይና ፡ በጀርመን ፡ በሌሎችም ፡ በኤውሮጳ ፡ አገሮችና ፡ አራዊት ፡ በተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ መኻከል ፡ ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነና ፡ የፌውዳል ፡ ጥንታዊ ፡ አገዛዝ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የተመለከታችሁት ፡ ይመስለኛል ።

፪ ፤ ጥቂት ፡ ብትመለከቱ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኤውሮጳ ፡ ጦርነትና ፡ ውጊያ ፡ በሚወዱ ፡ በብዙ ፡ ነገዶች ፡ የተከፋፈለች ፡ እንደ ፡ ነበረች ፤ እያንዳንዱም ፡ ነገድ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ነበረውና ፡ ንጉሡም ፤ በበታቹ ፡ የሾማቸው ፡ አያሎች ፡ ኀያላን ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፤ እነዚህም ፡ ኀያላን ፡ እያንዳንዱ ፡ ልክና ፡ ስፍር ፡ የሌለው ፡ (ዜጋ) ፡ ጢሰኛ ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፤ ልታስቡ ፡ ትችላላችሁ ።

፫ ፤ ንጉሡና ፡ መኳንንቱ ፤ በደንጊያ ፡ ከታነጠ ፡ ምሽግ ፡ ውስጥ ፡ መኖራቸውን ፡ አትዘንጉት ። እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ አያሎች ፡ ሥራዎች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኤውሮጳ ፤ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ይገኛሉ ፤ ከነዚህም ፡ አያሎቹ ፡ የተሠሩት ፡ ከሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ነው ። የሚበዙት ፡ ፈራርሰዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ጥንት ፡ የነበረው ፤ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሲተረክና ፡ ሲነገር ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ።

፬ ፤ የፌውዳል ፡ ጥንታዊ ፡ አገዛዝ ፡ ዐይነት ፡ የተጀመረበት ፡ እርግጡ ፡ አይታወቅም ። ነገር ፡ ግን ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ የነበሩ ፡ ነገድ ፡ መጀመሪያ ፡ ይህን ፡ አገዛዝ ፡ አቆሙና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍራንኮች ፡ የተባሉት ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳይ ፡ አገር ፡ አገቡት ። እነዚህም ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፬፻፹ ፡ ዓ. ም. ባገሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ በ፬፻፹፮ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ የፈረሳይን ፡ መንግሥት ፡ ያቆሙ ፡ ናቸው ። በሻርለማኝ ፡ ዘመን ፡ ኀይላቸው ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ነበር ፤ ከጥቂት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የኤውሮጳን ፡ ሁሉ ፡ ፖለቲካ ፡ መሥራቾች ፡ ሆኑ ።

፭ ፤ በፌውዳል ፡ ጊዜ ፤ (በጥንት ፡ አገዛዝ ፡ ጊዜ ፡) ክሮች ፡ ነገሥታትና ፡ ባሮን ፡ የሚባሉት ፡ የኀይልና ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ በስውር ፡ ማድረጋቸውን ፡ አልተውም ፤

አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ይኸው ፡ ባሮን ፡ የሚባለው ፡ እያዘነጋ ፡ በደካማው ፡ ላይ ፡ አደጋ፡ ይጥልና ፡ ምሽጉን ፡ ይይዝበታል ። ወይም ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ አግ ብቶ ፡ ይገድለዋል ። አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ አንዱ ፡ ባሮን ፡ የሌላውን ፡ ሹም ፡ ወይም ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ነጥቆ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ይወስድበታል ።

፮ ፤ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ይነቀፍ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ናይት ፡ ተብሎ ፡ የተሾመው ፡ ጀግና ፡ እንዲህ ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ እንዳይደረግ ፡ ይከላከላል ። ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ የግፍ ፡ ሥራ ፡ የሚ ሠሩ ፡ ሹማምት ፡ የተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይዋጋቸዋል ። ያለዚያ ፡ ደግሞ ፡ በግፍ ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የወሰዱት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ለተጐዳው ፡ እንዲመልሱ ፡ ያደርጋል ።

፯ ፤ ሕዝቡ ፡ ለነዚሁ ፡ ናይቶት ፡ እልል ፡ ይሉላቸው ፡ ነበር ፤ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ደፋሮች ፡ እንዲሆኑ ፡ ታላቅ ፡ ልዕልና ፡ ያደርጉላቸዋል ። እንዲህ ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያሉ ፡ ናይቶች ፡ እየበዙ ፡ ሄዱ ፡ በመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ጊዜም ፡ አያሎች ፡ ናይቶች ፡ መልካም ፡ ሥራቸውን ፡ አሳይተዋል ።

፰ ፤ በመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ጊዜም ፡ ናይቶች ፡ እንዲሾሙ ፡ እንደ ፡ ደንብ ፡ አድርገው ፡ የናይትነት ፡ ሹመትን ፡ ያጸኑት ፡ ይመስላል ፤ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከሺ ፡ ፩፻ ፡ ጀምሮ ፡ በኤውሮጳ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ የታወቀ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ መቆሙን ፡ እና ሳስባለን ።

፱ ፤ ናይት ፡ የሚሉት ፡ ማዕርግ ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ሹመት ፡ የሚቀበሉ ፡ ሁሉ ፡ ለሃይማኖት ፡ ለበጎና ፡ ለቅንነት ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ቆሙ ፡ ይታሰባል ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ በፍርድ ፡ በኩል ፡ ቢበደል ፡ ነገሩን ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መርምረው ፡ ወደ ፡ በጎነት ፡ ያቃኑለታል ። ማንም ፡ ጭንቅና ፡ ጒዳት ፡ የሚያገኘው ፡ ቢሆን ፡ እርሱን ፡ ለማዳን ፡ ሲሉ ፡ ሕይወታቸውን ፡ እስከ ፡ ማሳለፍ ፡ ይደርሳሉ ።

፲ ፤ ከዚህም ፡ በቀር ፡ ደግም ፡ እነዚሁ ፡ ናይት ፡ የሚባሉት ፡ ጀግኖች ፡ ሁለጊዜ ፡ የሚናገሩት ፡ እውነትን ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ መቸውንም ፡ ቢሆን ፡ የሰጡትን ፡ ተስፋ ፡ ይፈጽሙታል ፤ ሙሉ ፡ ቸርነትና ፡ ብርታት ፡ ያላቸው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ይታሰባሉ ። በማንኛውም ፡ በኩል ፡ አይበድሉም ። ባጭሩ ፡ እነርሱ ፡ በማንኛውም ፡ ችግር ፡ ቢሆን ፡ ለሰው ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ የሰው ፡ መድኀኒት ፡ ሊሆኑ ፤ ባላቸ ውም ፡ ኀይል ፤ ሰውን ፡ ሊረዱ ፡ የታጠቁ ፡ ናቸው ።

፲፩ ፤ ከነዚሁ ፡ ናይቶች ፡ አያሎቹ ፡ የተጠቃና ፡ የተጐዳ ፡ ሰው ፡ ለመፈለግ ፡ ሲሉ ፡ በአየገር ፡ ቤቱ ፡ እየዞሩ ፡ ዘመናቸውን ፡ ሁሉ ፡ ተኮርቻ ፡ ላይ ፡ ሳይወርዱ ፡ ይኖ ራሉ ። እነዚህም ፡ ናይት ፡ ኤራንት ፡ ይባላሉ ። በመንገድ ፡ ሲሄዱ ፡ ሳሉ ፡ አን ዳች ፡ ጒዳት ፡ ያገኘው ፡ ሰው ፡ ቢያገኙ ፡ ርዳታቸውን ፡ ሳያደርጉለት ፡ አያልፉም ።

፲፪ ፤ ተሰርቀው ፡ በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ የተዘጋባቸውን ፡ ሴቶች ፡ ለማዳን ፡ በተ ለይ ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ። ስለነዚህ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ። እውነት ፡ ነው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ናይቶች ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡

ሠርተው ፣ ይበድላሉ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ እንዲህ ፣ በማድረግ ፣ የበጎ ፣ ሥራ ፣ መሐ ላቸውን ፣ መተላለፍ ፣ ይሆንባቸዋል ።

ጥያቄ ።

፩ ፤ ኤውሮጳ ፣ በባለመሬቶች ፣ ዘመን ፣ ምን ፣ ይመስላችኋል ፣ ?
፪ ፤ ምን ፣ ይታሰባችኋል ?
፫ ፤ የመሬት ፣ መጋዘና ፣ የጢሰኝነት ፣ ደንብ ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ?
ወደ ፣ ፈረንሳይ ፣ ማን ፣ አገባው ፣ ? ምን ፣ ጊዜ ፣ ተለመደ ፣ ? የፈረን ሳይ ፣ ንጉሥ ፣ መግዛትን ፣ ማን ፣ አቆመው ፣ ?
የመሬት ፣ ደንብ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ዘመን ፣ ጸንቶ ፣ ቈየ ፣ ? እንደምን ፣ ተጀመረ ፣ ?
፬ ፤ (በፊውዳል ፣) በዚሁ ፣ ዘመን ፣ ምን ፣ ተደረገ ፣ ?
፭ ፤ እንዲህ ፣ ያለውን ነገር ፣ በምን ፣ አሰቡት ፣ ? ናይት ፣ የተባለው ፣ አንዳ ንድ ፣ ጊዜ ፣ ምን ፣ ያደርጋል ፣ ?
፮ ፤ ሕዝቡሳ ፣ ? ናይት ፣ የተባለውስ ፣ ?
፯ ፤ የመስቀል ፣ ጦርነት ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? ናይት ፣ ኤራንትሪ ፣ የሚሉት ፣ ዋና ፣ ሥርዓት ፣ ሆኖ ፣ የተገለጠው ፣ ምን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ?
፰ ፤ ይህን ፣ ሥራ ፣ የሚሠሩ ፣ እንዴት ፣ ሆኑ ፣ ?
፲ ፤ ለነዚሁ ፣ ለናይቶች ፣ የሚያስፈልጋቸውና ፣ የሚፈለግባቸው ፣ ምንድነው ፣ ?
፲፩ ፤ ናይት ፣ ኤራንት ፣ የተባሉት ፣ እነማን ፣ ኑሩዋል ፤ ?
፲፪ ፤ ለሌቶች ፣ ምን ፣ አደረጉ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፲፴፮ ፣ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፣ አያሎች ፣ ናይቶች ።

፩ ፤ አንዱ ፣ ናይት ፣ ከሌላው ፣ ጋር ፣ የተገናኘ ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ በጨዋታም ፣ ሆነ ፤ ወይም ፣ በምር ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ ወደ ፣ መዋጋት ፣ ይደርሳሉ ። ከነርሱም ፣ አንዳንዶቹ ፣ ዝና ፣ ለማግኘት ፣ ሲሉ ፣ ነው ። ሕዝቡም ፣ የነዚህኑ ፣ ሥራ ፣ ለማክበር ፣ ብለው ፣ በዘፈንና ፣ በእጕርጕሮ ፣ እያደረጉ ፣ ብዙ ፣ ግጥም ፣ ይገጥሙላቸዋል ።
፪ ፤ ናይቶች ፣ ጠንካራና ፣ ያማሩ ፣ ፈረሶች ፣ በመጋለብ ፣ የተለዩ ፣ ናቸው ። ከነ ዚህም አያሎች ፣ በታሪካቸው ፣ የታወቁ ፣ ናቸው ። ናይት ፣ የተባለ ፣ መቸው ንም ፣ የተሰናዳ ፣ የጦር ፣ መሣሪያ ፣ አለው ፤ ዋናው ፣ መሣሪያው ፣ ያማረ ፣ ጦር ፣ ነው ። ከዚህም ፣ ሌላ ፣ ሰይፍ ፤ ጩቤ ፤ መጥረቢያ ፤ ዱላ ፣ አለው ።
፫ ፤ በነዚህ ፣ መሣሪያዎች ፣ ላይ ፣ ለመመከቻ ፣ የሚሆን ፣ የብረት ፣ ጋሻ ፣ ከጥሩ ፣ ብረት ፣ የተሠራ ፣ የራስ ፣ ቁር ፣ ፊቱን ፣ ሁሉ ፣ ከሚሸፍንበት ፣ ጋር ፣ በሰውነቱ ፣ የሚለብሰው ፣ የብረት ፣ ልብስ ፤ ማጠፊያ ፣ ያለው ፣ ከብረት ፣ የተሠራ ፣ ሴዴሪያ ፣ የመሰለ ፤ ለመላው ፣ አካሉ ፣ የተስማማ ፣ ልብስ ፣ አለው ። ከዚህ ፣ ሁሉ ፣ ጋር ፣ ናይት ፣ የተባለ ፣ ከላይ ፣ እስከ ፣ ታች ፣ እስከ ፣ ተረከዙ ፣ ድረስ ፣ የተንቡዋለለ ፣ ቀሚስ ፣ ይደርባል ።

፬ ፤ ፈረሱም ፡ እንደዚሁ ፡ በጥንቃቄ ፡ የሚስማማው ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ አለው ። ራሱ ንና ፡ ደረቱን ፣ ጐንና ፣ ጐኑን ፡ የሚሸፍን ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ ያደርጉለታል ። እን ዲያውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመላው ፡ አካሉ ፡ ከጥሩ ፡ ብረት ፡ የተሠራ ፡ የሚያብለ ጨልጭ ፡ የብረት ፡ ልብስ ፣ ያደርጉለታል ። ፈረሶቻቸውን ፡ በመገራት ፤ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ በማሰናዳት ፡ እንደሚስማማቸውም ፡ በማድረግ ፡ በውነት ፡ ናይቶችን ፡ የሚመስላቸው ፡ የለም ።

፭ ፤ ለራሳቸው ፡ ጤንነትና ፡ ኀይል ፡ ለማግኘት ፡ ተግተው ፡ እንደሚጥሩ ፡ እንዲ ሁም ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ አዘውትረው ፡ ለመገራትና ፡ ለማስለመድ ፡ ትጋት ፡ አላቸው ።

፮ ፤ ሎቸውንም ፡ አንዱን ፡ ናይት ፡ ባለመዋሉ ፡ ወይም ፡ በለሚሎቹ ፡ ይከተሉታል ። እነዚህም ፡ ጌቶቻቸውን ፡ የሚከተሉ ፡ ባለሙዋሎች ፡ ተምረው ፡ በኋላ ፡ ናይቶች ፡ ይሆናሉ ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ። የችባልሪ ፡ ትምህርት ፡ እየገነነ ፡ ስለ ሄደ ፡ ከበሬታና ፡ ማዕርግ ፡ የሚገኝ ፡ ናይት ፡ በመሆን ፣ ብቻ ፡ ሆነ ፤ ስለዚህ ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፣ የጦር ፡ መሪዎችም ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ናይትነትን ፡ ለራሳቸው ፡ አደረ ጉት ፤ የመስቀል ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ የተከበሩ ፡ መሮች ፡ የነበሩት ፣ ከእንግሊዞች ፣ ሪካርድ ፡ ከፈረንሳዎች ፡ ጎድፍራይና ፡ ሌሎችም ፡ ናይቶች ፣ ተብለው ፡ ነበር ።

፯ ፤ በኋላ ፡ ስለ ናይቶች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ደንብ ፡ ተደረገና ፡ ሁሉም ፡ ለየራሱ ፡ ሥራት ፡ አወጣ ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ ናይቶች ፤ የማልታ ፡ ናይቶች ፤ የመስ ቀል ፡ ናይቶች ፣ የጌታን ፡ መቃብር ፡ ለመሳለም ፡ የሚመጡትን ፡ መናንያን ፡ የሚ ጠብቁ ፡ ናይቶች ፡ የሚባሉ ፡ ተደረጉ ።

፰ ፤ ሕዝብ ፡ ሲሠለጥን ፣ በአውሮጳ ፡ በልዩ ፡ በልዩ ፡ ስፍራ ፡ ለጨዋታ ፡ የመሰ ብሰብ ፡ ልማድ ፣ ነበራቸው ። በዚሁ ፣ ምክንያት ፡ ታላቅ ፡ የበዓል ፡ አደራረግ ፡ የሚያሳዩ ፡ ስለ ሆነ ፡ ይህንኑ ፣ ለማየት ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ይሰበሰብ ፡ ነበር ፤ በዚያ ፡ ሊነገር ፡ የማይቻል ፡ ብዙ ፣ ዐይነት ፡ የሚታይ ፡ ነገር ፡ ያሳዩ ፡ ነበር ፤ ይህንኑ ፡ በማየት ፡ ነገሥታትና ፣ መኳንንት ፣ ወይዛዝሮችም ፣ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ ነበር ።

፱ ፤ የተሰናዳ ፣ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ከለበሱት ፡ ናይቶች ፤ ጋር ፡ ገጥመው ፡ ውጊያ ፡ የሚያሳዩ ፣ ሰዎች ፡ ነበሩና ፣ ዙሪያውን ፡ ድንኳን ፡ ተተክሎ ፡ ተመልካቾች ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ አሉበት ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ሲሄዱ ፡ ለድል ፡ አድራጊ ፡ ናይቶች ፡ ሕዝቡ ፡ ያጨበጭቡላቸዋል ፤ ነገሥታትና ፡ ንግሥቶችም ፡ ሳያቀሩ ፡ የመውደድ ፡ ምልክት ፡ ያሳዩዋቸዋል ።

፲ ፤ የጀግኖች ፡ ትምህርት ፡ እንዲህ ፡ ነበር ፤ ጊዜ ፡ ናሮኝ ፡ ቢሆን ፡ ስለ ፡ ናይቶች ፡ ታሪክ ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ በጻፍኩ ፡ ነበር ፤ በጀግኖች ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ተረት ፡ ተጽፎአል ፣ ይህም ፡ የተከበሩት ፡ አሽናፎች ፡ ያደረጉትን ፡ ሥራ ፡ ያሳያል ፤ ከነዚህም ፡ ከተጻፉት ፡ ተረቶች ፡ አንድ ፡ አንዱ ፡ እጅግ ፡ የሚያሥቅ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉም ፡ የማይታመን ፡ ተረት ፡ የመላበት ፡ ነው ።

፲፩ ፤ (ቺቫልሪ) ፡ ጀግኖች ፡ ከሺ ፡ ፻፻ ፡ እስከ ሺ ፡ ፬፻ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ ነበሩ ። ከዚህ ፡ ከኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ጀምረው ፡ በፍጥነት ፡ እየተዋረዱ ፡ ሄዱና ፡ በኤልሳቤጥ ፡

በእንግሊዝ ፡ ንግሥት ፡ ዘመን ፡ ማለት ፡ በሺ ፡ ፮፻ ዓ. ም. ፈጽሞ ፡ ሥራቸው ፡ ቆመ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ለጨዋታ ፡ ብለው ፡ መሰብሰብ ፡ ቢያደርጉም ፡ ባለፈው ፡ በቀድሞው ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፡ ብለው ፡ ለመታሰቢያ ፡ ብቻ ፡ ያሳዩ ፡ ነበር ።

፲፪ ፤ ስለ ፡ ፊውዳል ፡ ሲስቲም ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ጥንት ፡ አገዛዝ ፡ ስለ ፡ መስቀል ፡ ጦርነትና ፡ ቺባልሪ ፡ ይኸው ፡ ነገርኋችሁ ። የዚያ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ በመሰለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚገኙ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የፈረንሳይን ፡ ታሪክ ፡ ጨምሬ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገርኋችሁ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሁለቱ ፡ ናይት ፡ ኤራን ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? በሥራቸው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ክብረት ፡ ተደረገ ፡ ?

፪ ፤ ፈረሶቻቸው ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? አንድ ፡ ናይት ፡ ሲሰለፍ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የፈረስ ፡ ዕቃው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? የናይት ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ ሲያስለምዱ ፤ ሲገሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፮ ፤ የናይት ፡ አሽከሮች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ? ናይት ፡ ለመሆን ፡ እንዴት ፡ ይታሰባል ፡ ?

በመስቀል ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የተከበሩ ፡ ናይቶች ፡ ማንና ፡ ማናቸው ፡ ስለ ፡ ናይቶች ፡ ደንብና ፡ ሥርዓት ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?

፰—፱ ፤ የጦር ፡ ትምህርታቸው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ገልጠህ ፡ ተናገር ።

፲ ፡ ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ሊነገርላቸው ፡ ይቻላልን ፡ ? ቺቫልሪ ፡ ገንኖበት ፡ የነበረው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

ከ፲፬፻ ዓ. ም. በኋላ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ቀረ ፡ ?

፲፪ ፤ የፊውዳል ፡ ሥርዓትና ፡ የቺባልሪ ፡ ታሪክ ፡ ለምን ፡ ተፈረንሳይ ፡ ታሪክ ፡ ጋር ፡ ተጋጠመ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፴፯ ፡ ኤውሮጳ ።

ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ፊሊጽና ፡ ስለ ፡ ጳጳስ (ቦኒፋኪዩስ ፡) ቦኒፈስ ።

ስለ ፡ ፈረንሳይና ፡ የእንግሊዝ ፡ ጦርነት ።

፩ ፤ አሁንም ፡ ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ የምነግራችሁን ፡ ታሪክ ፡ ገና ፡ አልጨረስሁም ። ከወፍ ራሙ ፡ ቻርልስ ፡ ሁፍ ፡ ኬፐትና ፡ ከመለከትኋቸው ፡ ከሌሎቹ ፡ ነገሥታት ፡ በኋላ ፡ አያሌች ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሺ ፡ ፪፻፹፪ ዓ. ም. ወደ ፡ ነገሠው ፡ ፊሊጽ ፡ ውቡ ፡ ወደ ፡ ተባለው ፡ እስከመጣ ፡ ድረስ ፡ እዘላቸዋለሁ ። ይህም ፡ ፊሊጽ ፡ የተባለ ፡ እጅግ ፡ ውብትና ፡ ቊንጅና ፡ ተሰጥቶት ፡ ሳለ ፡ አእምሮውና ፡ አሳቡ ፡ መጥፎ ፡ ነበር ። በርሱ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ የሆነ ፡ ነገር ፡ በጳጳስ ፡ ቦኒፋኪዩስና ፡ በርሱ ፡ መኻከል ፡ የሆነው ፡ ታላቅ ፡ ፀብ ፡ ነው ።

፪ ፤ የጽጽስና ፡ ማዕርግና ፡ ዘውድ ፡ ካገኙት ፡ አንዱ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ገዢ ፡ የነበረ ፡ ጳጳስ ፡ እርሱ ፡ ነው ። ከነገሥታት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ ሆኖ ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ እርሱ ፡ መሆኑን ፡ ለኤውሮጳ ፡ ነገሥታት ፡ አስታወቀ ። ነገር ፡ ግን ፡ ውቡ ፡ ፊሊጵ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ አልተቀበለምና ፡ አሻፈረኝ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ አላጸደቀለትም ። ንጉሡ ፡ ፊሊጵ ፡ ለጳጳስ ፡ ስለ ፡ አልታዘዘ ፡ ጳጳሱ ፡ ገዘተው ። ንጉሥ ፡ ፊሊጵም ፡ ለጳጳስ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ ሰጠው ።

፫ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ የፊሊጵ ፡ ወዳጆች ፡ የሆኑ ፡ ጳጳስ ፡ ቦኒፋኪዩስን ፡ ያዙና ፡ ከአሰሩት ፡ በኋላ ፡ ኮርቻ ፡ ሳይጭኑና ፡ ልጓም ፡ ሳይለጉሙ ፡ በሌጣ ፡ ፈረስ ፡ አስቀመጡ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ፈረሱ ፡ ጭራ ፡ ወገን ፡ አደረጉና ፡ እንዲጋልብ ፡ አደረጉት ፡ ያየው ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ የሚያሥቅ ፡ አደጋ ፡ ባቡኑ ፡ ላይ ፡ ደረሰበት ፡ እያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሥቅ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሚያሳዝነው ፡ ጳጳስ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ውርደትና ፡ መሣቂያ ፡ መሆኑ ፡ ገንዘቡንም ፡ መዘረፉ ፡ በውነት ፡ ገደለው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፊሊጵ ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ በጤና ፡ ኖረ ።

፬ ፤ መቸውንም ፡ ፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ ወዳጅ ፡ ሕዝብ ፡ ነውና ፡ ከእንግሊዞች ፡ ጋር ፡ ሁልጊዜ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ። እንግሊዞችና ፡ ፈረንሳዎች ፡ ከጥንቱ ፡ ጠላት ፡ ሁነው ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበር ። ዛሬ ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ ተለዋውጦአል ።

፭ ፤ አራተኛ ፡ ካርል ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በሺ ፡ ፫፻፳፰ ፡ የቫሎስ ፡ ፊሊጵ ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ የኤድዋርድ ፡ ፫ኛ ፡ እናት ፡ የውቡ ፡ ፊሊጵ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሆነች ፡ በፈረንሳይ ፡ ዙፋን ፡ ለመቀመጥ ፡ የሚገባው ፡ ንጉሥ ፡ እርሱ ፡ መሆኑን ፡ አረጋገጠና ፡ የእንግሊዝን ፡ ጦር ፡ ሰብስቦ ፡ ፈረንሳይን ፡ ለመውረር ፡ ምኞቱን ፡ አበረታ ።

፮ ፤ ንጉሥ ፡ ኤድዋርድ ፡ የቫሎስ ፡ ፊሊጵን ፡ እኔና ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እንዋጋና ፡ ይዋጣልን ፡ ቢለው ፡ ፊሊጵ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱን ፡ ይዞ ፡ መግጠሙን ፡ መረጠና ፡ በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ ክሬሲ ፡ በተባለ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ በሺ ፡ ፫፻፵፮ ፡ ዓ. ም. ተዋግተው ፡ ከፈረንሳይ ፡ ወገን ፡ አያሎች ፡ ጀግኖች ፡ መኳንንቶችና ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ቀሩ ።

፯ ፤ በሺ ፡ ፫፻፶ ፡ ጆን ፡ መልካሙ ፡ የተባለ ፡ የቫሎስ ፡ ፊሊጵ ፡ ልጅ ፡ በፈረንሳይ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ፤ የኤድዋርድ ፡ ሦስተኛ ፡ ታላቁ ፡ ልጅ ፡ የእንግሊዝን ፡ ጦር ፡ አስከተተና ፡ አገሪቱን ፡ ፈረንሳይን ፡ ወረራት ፤ የርሱም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ጥቍር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ ይሉት ፡ ነበር ።

፰ ፤ ጆን ፡ ያፈረሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ስድሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ይዞ ፡ ፑዋክቴር ፡ አጠገብ ፡ የእንግሊዝን ፡ ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ ተገናኘው ። ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ወታደሮች ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ ነበርና ፡ እንግሊዞችም ፡ በፈረንሳዎች ፡ ላይ ፡ ቀሥታቸውን ፡ ገትረው ፡ ይነድፉዋቸው ፡ ጀመሩ ፤ ታላቅ ፡ ውጊያም ፡ ከአደረጉ ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ ጆን ፡ ተያዘና ፡ ምርኮኛ ፡ ሆኖ ፡ በሎንዶን ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ።

፱ ፤ ካርል ፡ ጠቢቡ ፡ ባባቱ ፡ በጆን ፡ መልካሙ ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ። ኤድዋርድ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ አረጀና ፡ ልጁም ፡ ጀግናው ፡ ጥቍር ፡ ፕሪንስ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ፈረንሳዎች ፡ ካሊስ ፡ ከምትባልው ፡ ከተማ ፡ በቀር ፡ እንግሊዝ ፡ አሸንፎ ፡ ይዞባቸው ፡ የነበረውን ፡ ግዛታቸውን ፡ ሁሉ ፡ መልሰው ፡ እጅ ፡ አደረጉ ።

፲ ፤ ግን ፡ ካርል ፡ የተወደደ ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እንግሊዞች ፡ እን ደገና ፡ ጦርነት ፡ ፈለጉ ፤ በኋላ ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የነገሠው ፡ ሄንሪ ፡ ፭ኛ ፡ ፈረን ሳይን ፡ ወረራት ። አጊንኮርት ፡ በተባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሲዋጉ ፡ እንግሊዞች ፡ ፲፭ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡ ሳሉ ፡ ፈረንሳዎች ፡ ቅርብ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ይዘው ፡ ነበር ።

፲፩ ፤ ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንግሊዞች ፡ አርባ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ሲሞቱባቸው ፡ የከበረ ፡ ድልን ፡ አገኙ ። ከፈረንሳይ ፡ ወገን ፡ የፈረንሳይ ፡ የሰላም ፡ መሪዎች ፡ የነበሩ ፡ ሰባት ፡ መኳንንትና ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱባቸው ። ይኸውም ፡ ከብዙ ፡ ምር ኮኞች ፡ በቀር ፡ ነው ፤ በሺ ፡ ፬፻፳ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በእልልታ ፡ ወደ ፡ ፓሪስ ፡ ገባ ።

፲፪ ፤ ግን ፡ ወዲያው ፡ ሳይዘገይ ፡ ሄንሪ ፡ የእንግሊዝ ፡ ንጉሥ ፡ ሞተ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ፈረንሳዎች ፡ እንግሊዞችን ፡ ማሸነፍ ፡ ጀመሩ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የፈረንሳይ ፡ መሪ ፡ የአርሌንስ ፡ ጆን ፡ ሜድ ፡ የተባለች ፡ ያ፲፰ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረች ። ይህችም ፡ እጅግ ፡ ቆንጆ ፡ ነበረች ፤ ፈረንሳዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንግሊዝ ፡ ወራሪ ፡ ሊያ ድናቸው ፡ ፈልጎ ፡ ይህችን ፡ እንደላከላቸው ፡ ያምኑ ፡ ነበሩ ። እንግሊዞች ፡ ግን ፡ ሴት ፡ ውሻ ፡ እንደ ፡ ነበረችና ፡ እርሱዋንም ፡ የሚረዳ ፡ ሁሉ ፡ ጠላታቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ያምኑ ፡ ነበሩ ።

፲፫ ፤ ለጊዜው ፡ አያል ፡ ወራት ፡ ያህል ፡ ቅድስት ፡ የአርሌንስን ፡ ጆን ፡ ማንም ፡ ሊቋቋማት ፡ አልተቻለውም ፡ ከጥሩ ፡ ብረት ፡ የተሠራ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፤ ንጣቱ ፡ በረዶ ፡ የመሰለ ፡ አምባላይ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጣ ፤ በፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ ፊት ፡ ትታይ ፡ ነበር ። በእጅዋም ፡ የመድኀኒታችን ፡ ሥዕል ፡ የተሣለበት ፡ ቅዱስ ፡ ባንዴራ ፡ ይዛ ፡ ነበረች ። ዳሩ ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ከጦርነቱ ፡ ቈስላ ፡ ተማረከች ። እንግሊዞች ፡ ጠን ቋይ ፡ ሟርተኛ ፡ ነች ፡ ብለው ፡ በሕይትዋ ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ ገብታ ፡ ተቃጥላ ፡ መሞት ፡ ይገባታል ፡ ብለው ፡ ፈረዱባት ።

፲፬ ፤ እንዲሁም ፡ ሩን ፡ በሚባል ፡ ገብያ ፡ አ ቍጥተው ፡ ባንድ ፡ ዕንጨት ፡ አሠሩ ዋት ፤ በዙሪያዋ ፡ የተከመረው ፡ ዕንጨት ፡ ሲቃጠል ፡ ነበልባሉ ፡ ድምፅ ፡ እየ ሰጠ ፡ ሲተምና ፡ ሲያፋዋጭ ፡ እየሰሙ ፡ የእንግሊዝ ፡ ጭፍሮች ፡ ደስ ፡ ብሎዋቸው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ እሳቱ ፡ ተቃጥሎ ፡ ሲያልቅ ፡ ካመድና ፡ ከአርሌንስ ፡ ጆን ፡ ሜድ ፡ ነጭ ፡ አጥንት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የቀረ ፡ የለም ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ሡቡ ፡ ፊሊጵ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነገሠ ፡ ? ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፪ ፤ ጳጳስ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ? ፡ በርሱና ፡ በፊሊጵ ፡ መኻከል ፡ ምን ፡ ነበረ ፡ ?

፫ ፤ ፊሊጵ ፣ በቦኒፋኪዩስ ፣ ላይ ፣ ያደረገው ፣ ምንድነው ፣ ?
በጳጳሱ ፣ ላይ ፣ ባደረገው ፣ ነገር ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፬ ፤ ፈረንሳይ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ? እንግሊዞችና ፣ ፈረንሳዎች ፣ በምንነት ፣ ይተሳሰቡ ፣ ነበር ፣ ?

፭ ፤ ቻርልስ ፣ ፬ኛ ፣ መቼ ፣ ሞተ ፣ ? ፣ ፊልጵ የቫሎሱ ፣ መቼ ፣ ነገሠ ፣ ?

፮ ፤ ኤድርዋድ ፣ ሦስተኛ ፣ ስለምን ፣ ተፋለመው ፣ ?

፯ ፤ ንጉሡ ፣ ኤድዋርድ ፣ ምን ፣ አደረገ ፣ ? የክረሲ ጦርነት ፣ እዴት ፣ ሆነ ፣ ?

፰ ፤ በ፲፫፻፶ ፣ ማን ፣ ነገሠ ፣ ?

፱ ፤ ጥቍር ፣ ፕሪንስ ፣ የተባለ ፣ ማነው ፣ ?
ጥቍር ፣ ፕሪንስን ፣ የተቋቋመው ፣ ማነው ፣ ? ስለ ፣ ጦርነቱ ፣ ተናገር ።

፲ ፤ ጆን ፣ መልካሙ ፣ የተባለውን ፣ ማን ፣ ወረሰው ፣ ?
ፈረንሳዎች ፣ የነርሱ ፣ ግዛት ፣ የነበረውን ፣ ከእንግሊዞች ፣ እንደ ፣ ገና ፣
መልሶ ፣ ለመያዝ ፣ እንደምን ፣ ቻሉ ፣ ?

፲፩ ፤ ከዚህ ፣ ቀጥሎ ፣ የነበረው ፣ የፈረንሳይ ፣ ንጉሥ ፣ ማነው ፣ ?

፲፪ ፤ ከሄንሪ ፣ ፭ኛ ፣ ጋር ፣ የተዋጋው ፣ የምን ፣ ጦር ፣ ነው ፣ ?
የትኛው ፣ ወገን ፣ አሸነፈ ፣ ?
ከፈረንሳይ ፣ ወገን ፣ የረገፉ ፣ ምን ፣ ያህል ፣ ናቸው ፣ ?
በ፲፬፻፳ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?

፲፫ ፤ ከሄንሪ ፣ ፭ኛ ፣ ሞት ፣ በኋላ ፣ ምን ፣ ሆነ ፣ ?
የኦርሌንስ ፣ ሚድ ስለ ፣ ተባለችው ፣ ቆንጆ ፣ ተናገር ።
እንግሊዞችና ፣ ፈረንሳዎች ፣ ስለ ፣ ርስዋ ፣ ምን ፣ አሰቡ ፣ ?

፲፫ ፤ እንደ ፣ ምን ፣ የጦር ፣ መሪ ፣ ሆና ፣ ታየች ፣ ?

፲፬ ፤ የሚያሳዝን ፣ የዕድልዋ ፣ ፍጻሜ ፣ እንዴት ፣ ሆነ ፣ ?

## ምዕራፍ ፣ ፻፴፰ ።

### ስለ ፣ አያሎች ፣ የፈረንሳይ ፣ ነገሥታት ።

፩ ፤ ነገር ፣ ግን ፣ ፈረንሳዎች ፣ ምንም ፣ የነርሱ ፣ ካፒቴን ፣ የኦርሌንስ ፣ ሜድ ፣ ባትኖር ፣ ቀንቶዋቸው ፣ ድል ፣ አግኝተዋል ። እንግሊዞችም ፣ ሂንሪ ፣ አምስተኛ ፣ የያዘውን ፣ አገር ፣ ሁሉ ፣ አጡ ። የፈረንሳይ ፣ ንጉሥ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ እየተዋጋ ፣ ድል ፣ አድራጊ ፣ ስለ ፣ ሆነ ፣ ካርል ፣ ድል ፣ አድራጊው ፣ ይባል ፣ ነበር ።

፪ ፤ ይሁን ፣ እንጂ ፣ ርሱ ፣ ደስታ ፣ የሌለው ፣ ንጉሥ ፣ ነበር ፤ የገዛ ፣ ልጁ ፣ ጠልቶት ፣ በመርዝ ፣ ሊገድለው ፣ ሸምቆበት ፣ ነበር ፤ ይህም ፣ ዱለት ፣ ከተሰማ ፣ በኋላ ፣ ሽማግሌው ፣ ንጉሥ ፣ መርዝ ፣ ያቀምሱኛል ፣ ብሎ ፣ ስለ ፣ ፈራ ፣ ሕይወቱን ፣ ለመጠበቂያ ፣ ያህል ፣ የሚበቃ ፣ ምግብ ፣ ለመቅመስ ፣ እቅቶት ፣ እንዲህ ፣ ተቸግሮ ፣ በሚያሳዝን ፣ ሞት ፣ ሞተ ።

፫፤ ልጁ ፲፩ኛ፡ሉዊስ፡የተባለ፡በሺ፡፬፻፷፩፡በባቱ፡ዙፋን፡ተቀመጠ። ይህም፡ተንኰለኛና፡ክፉ፡ጨካኝ፡ንጉሥ፡ነበር፤ አንድ፡ጊዜ፡አንድ፡የከበረ፡ሰውዬ ተፈርዶበት፡አንገቱን፡በተቈረጠ፡ጊዜ፡ያባታቸውን፡ደም፡እንዲረጩ፡ልጆቹ፡ከመረባርቡ፡በታች፡ይቀመጡ፡ብሎ፡አዘዘ ።

፬፤ ከፈረንሳይ፡ነገሥታት፡እጅግ፡ስመ፡ጥሩ፡ተብሎ፡የታወቀው፡ፍራንሲስ፡አንደኛ፡በዙፋን፡የተቀመጠው፡በሺ፡፭፻፲፭፡ዓ. ም. ነው። ተስዊስና፡ተጀርመን፡ጋር፡ተዋግቶአል። ነገር፡ግን፡ፓቪያ፡ላይ፡በተዋጉ፡ጊዜ የጀርመን፡ንጉሥ፡ነገሥት፡ማርኮ፡አስቀመጠው ።

፭፤ ፍራንሲስ፡፩ኛ፡በነገሠ፡ዘመን፡በካሌስ፡አጠገብ፡ከእንግሊዝ፡ንጉሥ፡ጋር፡የፍቅር፡ግንኙት፡አደረገ፡እንጂ፡በመኻከላቸው፡ምንም፡ጠብ፡አልነበረም፤ በሁለቱም፡ወገን፡ደስ፡የሚያሰኝ፡መታየት፡ነበር፤ የተገናኙበትም፡ሜዳ፡የወርቅ፡ሜዳ፡ተብሎ ተሰየመ ።

፮፤ በሺ፡፭፻፷፡ክርል፡ዘጠነኛ፡የፈረንሳይ፡ንጉሥ፡ሆነ። ይህም፡የዘጠኝ፡ዓመት፡ልጅ፡ነበር፤ የርሱ፡መንግሥ፡በታሪክ፡ደም፡የመላበት፡እንደ፡ሆነ፡ይታያል። ያም፡ቀን፡የቅዱስ፡በርቶሎሜዎስ፡መተራረድ፡ይባላል ።

፯፤ የሮም፡ጳጳስ፡ወገኖች፡የሆኑት፡ካቶሊኮች፤ በመላ፡ፈረንሳይ፡ውስጥ የነበሩትን፡የሮምን፡ጳጳሳት፡የሚጠሉ፡ፕሮቴስታንቶችን፡ለመፍጀት፡ዶልተው፡ነበሩ። የቅዱስ፡በርተሎሜዎስ፡ዕለት፡በሺ፡፭፻፸፪፡ክፉ፡አሳባቸው፡ሰውን፡በመግደል፡ተፈጸመ፤ አያሌች፡ታሪክ፡ጸሐፊዎች፤ በዚያን፡ቀን፡መቶ፡ሺሕ፡ፕሮቴስታንቶች፡ታርደዋል፡እያሉ፡አረጋግጠው፡ጽፈዋል ።

፰፤ ንጉሡ፡ራሱ፡ጠመንጃውን፡ይዞ፡በቤተ፡መንግሥቱ፡መስኮት፡ተቀምጦ፤ በነዚህ፡በሚያሳዝኑ፡ምስኪናች፡እየተኰሰ፡ይገድል፡ነበር። ዳሩ፡ግን፡የኃጢአቱን፡ዋጋ፡እንዲቀበል፡ወዲያው፡በቶሎ፡ተጠራ። ይህን፡ያህል፡ሰው፡ከታረደ፡በኋላ፡በደዌ፡ተሣቀየና፡በሺ፡፭፻፸፬፡ሞተ ።

፱፤ ቀጥሎ፡የነገሠው፡ሂንሪ፡፬ኛ፡ነው፤ እርሱም፡በሺ፡፭፻፹፱፡ነገሠ፡ደግ፡ንጉሥ፤ ጀግናና፡አርበኛ፤ ቸር፡ሰው፡ስለ፡ነበር፡ዜጎቹ፡ይወዱት፡ነበር፤ ፈረንሳዎች፡ኩራታቸው፡በሂንሪ፡፬ኛ፡ነበር ።

፲፤ ይሁን፡እንጂ፡የሕዝቡ፡ፍቅር፡ሕይወቱን፡ለማዳን፡አልቻለም። አንድ፡ቀን፡በሠረገላው፡ተቀምጦ፤ በፓሪስ፡አደባባይ፡ሲንሸረሸር፡፭ቱ፡ባለሙዋሎቹ፡አብረውት፡ነበሩ፤ ሌላ፡ሠረገላ፡በመንገድ፡ሲመጣ፡ጊዜ፡ነጂው፡ፈረሶቹን፡ለማቆም፡ግድ፡ሆነበት፤ አሽከሮቹ፡ግን፡እስከዚያው፡ድረስ፡ሠረገላው፡ሳያልፍ፡እንዲደርሱበት፡በቋራጭ፡መንገድ፡ሄዱ ።

፲፩፤ በሠረገላው፡አጠገብ፡ንጉሡን፡ለመግደል፡ምቹ፡ጊዜ፡የሚጠብቅ፡ራቢላክ፡የተባለ፡ሰው፡ስለ፡ነበረ፡አሽከሮቹና፡ዘበኞቹ፡ትተውት፡ሄደው፡ብቻውን፡እንደ፡ሆነ፡በየ፡ጊዜ፡ጩቤውን፡መዘዘና፡ንጉሡን፡ወጋው፤ የፈረንሳይ፡ኃይል፡ሁሉ፡በዚያን፡ጊዜ፡ምንም፡አልጠቀመውም፤ የመጀመሪያው፡ጩቤ፡አቈሰለው፤ የሁለተኛውም፡ገደለው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ ? እንግሊዞችሳ ፡ ? የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፪ ፡ ድል ፡ አድራጊው ፡ ቻርልስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፫ ፤ ሉዊስ ፡ ፲፩ኛ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፬ ፤ ፍራንሲስ ፡ ፩ኛ ፡ በዙፋን ፡ የተቀመጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፭ ፡ በካሊስ ፡ የተደረገውን ፡ መገናኘት ፡ ተናገር ።
፮ ፤ ቻርልስ ፡ ዘጠነኛ ፡ የተባለ ፡ ወደ ፡ ዙፋን ፡ የቀረበው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
፯ ፤ የቅዱስ ፡ በርተሎሜዎስ ፡ መተራረድ ፡ የሚባለውን ፡ ተርከልን ።
፰ ፤ ቻርልስ ፡ ዘጠነኛ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?
፱ ፤ ሂንሪ ፡ አራተኛ ፡ በዙፋን ፡ የተቀመጠው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፲፩ ፤ እንዴ ፡ ምን ፡ ሕይወቱን ፡ አጣ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፲፻፱ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ መንግሥና ፡ ስለ ፡ ወራሾቹ ።

፩ ፤ በተገደለው ፡ ባራተኛው ፤ ሂንሪ ፡ ዙፋን ፡ ሉዊስ ፡ ፲፫ኛ ፡ ተቀመጠ ። የበለጠው ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅና ፡ ዲሬክተር ፡ ካርዲናል ፡ ሪሻልዩ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የራሱን ፡ ክብር ፡ ፈላጊ ፡ ቄስ ፡ ነበር ፤ ከንጉሡ ፡ ይልቅ ፡ እያደር ፡ የርሱ ፡ ኀይል ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ።

፪ ፤ ቀጥሎ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ ሉዊስ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ነበር ። እርሱም ፡ ፈረንሳዎች ፡ ታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ የሚሉት ፡ ነው ። ኵሩ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ፤ የርሱ ፡ ብግር ፡ ፈረንሳይን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ አገር ፡ ለማድረግ ፡ ነበር ። ከሌሎች ፡ ነገሥታት ፡ ይልቅ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ ለማድረግ ፡ አሰበ ፤ እንጂ ፡ ለሕዝቡ ፡ አኑዋኑዋር ፡ ትንሽም ፡ አሳብ ፡ አልነበረውም ።

፫ ፤ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ የሚያሥቅ ፡ አካሄድ ፡ ነበረው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በንጉሥ ፡ ያለው ፡ ታላቅነት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ይታሰባል ። በብልሀት ፡ የተሠራ ፡ ልክ ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ጠጕር ፡ የሚመስል ፡ የተቈላመመ ፡ ጠጕር ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ያንን ፡ ሳያደርግ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ አያየውም ። መጋረጃውን ፡ ጋርዶ ፡ ወደ ፡ መኝታው ፡ ካልገባ ፡ ያንን ፡ ከራሱ ፡ አውጥቶ ፡ አያውቅም ።

፬ ፤ በተወለደ ፡ በ፭ ፡ ዓመቱ ፡ ነገሠ ፤ መላው ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ከሰባ ፡ ሁለት ፡ ዓመት ፡ አያንስም ፤ ዘወትር ፡ ከጦርነት ፡ ተለይቶ ፡ ዐያውቅም ፤ በነገሠ ፡ በመጀመሪያ ፡ ዘመን ፡ የርሱ ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ግሩም ፡ የሆነ ፡ ድልን ፡ አግኝቶአል ።

፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በሽመገለበት ፡ ጊዜ ፡ የርሱን ፡ ጦር ፡ የእንግሊዝ ፡ ዱክ ፡ ድል ፡ አደረገና ፡ ከግዛቱ ፡ ቀንሶ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ አመጣበት ፡ የፈረንሳይም ፡ ሕዝብ ፡ በታላቁ ፡ ንጉሣቸው ፡ ምክንያት ፡ እየደከሙ ፡ ሄዱ ።

፯ ፤ በርሱ ፡ ምክንያት ፡ መድከማቸው ፡ ለዘመቻ ፡ ያለ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ስለ ፡ ወሰዱ
ባቸው ፡ ነው ። ሕዝቡ ፡ እንጀራ ፡ ከሚያገኙ ፡ ይልቅ ፡ የርሱ ፡ ክብር ፡ ማግኘት ፡
አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየው ፡ ነው ።

፰ ፤ በመጨረሻው ፡ በሺ ፡ ፲፯፻፲፭ ፡ ሽማግሌው ፡ ንጉሥ ፡ ሞተ ፡ በሕይወቱ ፡
ታላቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ እንደሚቻል ፡ ያህል ፡ ታላቅነቱን ፡
እንደ ፡ ያዘ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ የሚሄድ ፡ መሰላቸው ፤ ስለዚህ ፡ የሚታይ ፡ ፍት
ሐት ፡ አደረጉለት ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ በሚያልፉበት ፡ ሁሉ ፡ ንጉሡ ፡ በደንጊያ ፡ ሳይወገር ፡
ሞቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሬሳውን ፡ መውገር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እያ
ፏዋጩ ፡ የንጉሡን ፡ ሬሳ ፡ ይረግሙ ፡ ነበር ፤ የታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ መንግሥት ፡ እን
ደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ተፈጸመ ።

፲ ፤ የታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ ልጆችና ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ስለ ፡
ሞቱ ፡ የልጁ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ሉዊስ ፡ ፲፭ኛ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡
ዙፋኑን ፡ ወረሰ ።

፲፩ ፤ ሕፃኑ ፡ ንጉሥ ፡ አድጎ ፡ በእጁ ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ እስኪጨብጥ ፡ ድረስ ፡
የኦርሊን ፡ ዱክ ፡ የፈረንሳይን ፡ መንግሥት ፡ እንደራሴነት ፡ ያዘ ። ይህም ፡ ሰው ፡
ክፉ ፡ ነበር ፤ ዜጎቹ ፡ በሁለመናው ፡ ተከናውኖላቸው ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ እንዲሆኑ ፡
ለማድረግ ፡ ሕፃኑን ፡ ንጉሥ ፡ በማስተማር ፡ ፈንታ ፡ እንዲያውም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡
ክፉት ፡ ምሳሌ ፡ አደረገው ።

፲፪ ፤ ሉዊስ ፡ ፲፭ኛ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ታሰበው ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ፤ አምሳ ፡ ዘጠኝ ፡
ዓመት ፡ ሲገዛ ፡ ዘመኑን ፡ ሁሉ ፡ የራሱን ፡ ጥቅምና ፡ ደስታ ፡ ከመፈለግ ፡ በቀር ፡
ሌላ ፡ ምንም ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ የለም ።

፲፫ ፤ አገዛዙ ፡ የተበላሸ ፤ ዜጎቹም ፡ የተራቡ ፡ ነበሩ ፤ አገሩን ፡ ፈረንሳይንና ፡ ሕዝ
ቡን ፡ ምድር ፡ ተናውጦ ፡ ቢውጣቸው ፡ እንኳ ፡ ንጉሡ ፡ ምንም ፡ አይጠጠትም ።
የዚህ ፡ የተጠላ ፡ ሰው ፡ መንገሥ ፡ ንጉሥ ፤ የሚባለውን ፡ ቃል ፡ ለመጥላት ፡ ፈረ
ንሳዎችን ፡ አሰናዳቸው ፤ በሺ ፡ ፲፯፻፸፬ ፡ ሞተና ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ ሉዊስ ፡ ፲፮ኛ ፡
የኻያ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ሳለ ፡ ነገሠ ።

፲፬ ፤ በትዕቢተኛው ፡ በሉዊስ ፡ ፲፬ኛና ፡ በክፉው ፡ በሉዊስ ፡ ፲፭ኛው ፡ ምክንያት ፡
የፈረንሳይ ፡ ዓመፅ ፡ የሚባለው ፡ ተመሠረተ ። የዚህንም ፡ ታሪክ ፡ በሚመጣው ፡
ምዕራፍ ፡ እነግራችኋለሁ ።

፲፭ ፤ የዚያን ፡ የክፉውን ፡ ዘመን ፡ ታሪክ ፡ ልዘለው ፡ እወድ ፡ ነበር ፤ ይህን ፡
የደም ፡ መፍሰስ ፡ ታሪክ ፡ ያለበትን ፡ በማንበብ ፡ መጽሐፌን ፡ የሚመለከቱ ፡
ደስ ፡ እንደሚላቸው ፡ ዐውቃለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ የታሪክ ፡
ብርሃን ፡ ገጽ ፡ እንደ ፡ ተመለከትን ፡ እንዲሁም ፡ ጨለማውንና ፡ ደስ ፡ የማያሰኘ
ውንም ፡ ታሪክ ፡ ማንበብ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑ ፡ ስለ ፡ ታየኝ ፡ ነው ።

፲፭ ፤ በክሮች ፡ ገዦች ፡ ምክንያት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ጉዳት ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ እንደ መጣ ፡ በፈረንሳይ ፡ ዓመፅ ፡ የሆነውን ፡ እንመለከታለን ። ከተማሮቹ ፡ እኩሌቶቹ ፡ አድገው ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ገዦችን ፡ ለመምረጥ ፡ እንዲረዱ ፡ በተጠሩ ፡ ጊዜ ፡ መልካሙን ፡ ለመምረጥ ፡ የሚገባቸው ፡ መሆኑ ፡ ይሰማቸዋል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ አራተኛውን ፡ ሂንሪ ፡ ማን ፡ ወረሰው ፡ ? ካርዲናል ፡ ሪሽልዩ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፪ ፤ ቀጥሎ ፡ የነገሠው ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ ? ስለ ፡ ታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ ምን ፡ ትላለህ ፡ ?
፫ ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋግቶ ፡ ምን ፡ አገኘ ፡ ?
፬ ፤ ዱክ ፡ ማርልበሩ ፡ የተባለ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፭ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፮ ፡ ታላቁ ፡ ሉዊስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፤ ስለ ፡ ፍትሐቱ ፡ ተናገር ።
፯ ፤ ሉዊስ ፡ ፲፭ኛውን ፡ ማን ፡ ወረሰው ፡ ?
፰ ፤ የኦርሊን ፡ ዱክ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፩ ፤ ሉዊስ ፡ ፲፭ኛ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፪ ፤ ምን ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፱፻ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፡ ፈረንሳይ ፡ ዓመፅ ።

፩ ፤ ሉዊስ ፡ ፲፮ኛ ፡ ሕዝብን ፡ ለመግዛት ፡ የበቃ ፡ ስጦታ ፡ አልነበረውም ፡ እንጂ ፡ ልበ ፡ ቅን ፡ ቸር ፡ አሳቡ ፡ የተካከለ ፡ ሰው ፡ ነበር ፤ ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ የተሻለ ፡ ንጉሥ ፡ ለመሆን ፡ ይችል ፡ ነበር ። ግን ፡ መልካም ፡ ለማድረግ ፡ ካልቻለ ፤ እንዲሁም ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ አይችልም ።

፪ ፤ ንጉሡም ፡ የኦስትሪያን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሜሪ ፡ አንቱዋኔት ፡ የተባለችውን ፡ አገባ ፡ ይህችም ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ ጥሩ ፡ ቆንጆ ፡ ነበረች ። ነገር ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ የፈረንሳይን ፡ ሕዝብ ፡ አትወድም ፡ ነበር ።

፫ ፤ ይህ ፡ ንጉሥና ፡ ይህች ፡ ንግሥት ፡ ወዲያው ፡ እንደ ፡ ነገሡ ፡ በአሜሪካ ፡ ዓመፅ ፡ ተነሣ ፤ ዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ነጻነት ፡ ያለው ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ የሚኖር ፡ ሬፑብሊክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አወጀ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብም ፡ አሜሪካ ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ወደዱትና ፡ በንጉሥ ፡ ተመገዛት ፡ ይልቅ ፡ በሬፑብሊክ ፡ መገዛት ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ አሰቡ ።

፬ ፤ እነርሱንና ፡ አባቶቻቸውን ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ የነበረውን ፡ የንጉሥ ፡ አገዛዝ ፡ ለአሜሪካኖች ፡ ደስታንና ፡ መከናወንን ፡ ካመጣላቸው ፡ ከነጻነት ፡ አገዛዝ ፡ ጋር ፡ ማወዳደር ፡ ጀመሩ ፤ በነገሩ ፡ እጅግ ፡ አሰቡበት ፡ አብልጠው ፡ ሲያስቡበት ፡ ግን ፡ በሁኔታቸው ፡ ደስታ ፡ የላቸውም ፡ ነበር ።

፭ ፤ ባገር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ ደንባሪ ፡ ነው ። መላ ፡ ሕዝቡ ፡ ያበደ ፡ ወይም ፡ ያለመጠን ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ የሰከረ ፡ ይመስላል ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ የሆነው ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። ንጉሡንና ፡ ንግሥቲቱን ፤ ክቡራኑንና ፡ ካህናቱን ፤ ጨዋውንና ፡ ቀድሞ ፡ የሚያከብሩዋቸውን ፡ ሁሉ ፡ አምላካቸውን ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ተሳደቡ ።

፮ ፤ በሺ ፡ ፲፯፻፹፱ ፡ በፓሪስ ፡ የተደረገው ፡ የሕዝቡ ፡ ዓመፅ ፡ ባሲቲልን ፡ አፈራረሰው ። ባሲቲል ፡ ማለት ፡ ጥንት ፡ የፈረንሳይ ፡ ነገሥታት ፡ ግዞተኞቻቸውን ፡ እያገቡ ፡ የሚያስሩበት ፡ የጥንት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ ነው ። እየተፈረደባቸው ፡ በባሲቲል ፡ የእስር ፡ ቤት ፡ እየገቡ ፡ የታሠሩ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተገቡ ፡ በላይ ፡ ዳግመኛ ፡ የፀሓይን ፡ ብርሃን ፡ አያገኙም ።

፯ ፤ የባሲቲል ፡ መፍረስ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፤ ደግሞ ፡ በመጀመሪያ ፡ በፈረንሳይ ፡ ዓመፅ ፡ ሌሎችም ፡ እንደዚሁ ፡ ተደርገዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የጥንቱን ፡ መንግሥት ፡ ተገለበጡት ፡ ወዲያ ፡ መቆሚያቸው ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አላወቁትም ።

፰ ፤ የሰው ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ጎርፍ ፡ የሚፈስበት ፡ ሰዓት ፡ አልዘገየም ፤ የነጻነት ፡ ቆብ ፡ የሚሏትን ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ሳይለጥፍ ፡ የተገኘ ፡ ወንድ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ሕይወቱን ፡ ያጣ ፡ ነበር ።

፱ ፤ ያመፁት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ በፓሪስ ፡ አደባባይ ፡ የሰውን ፡ ራስ ፡ በዕንጨት ፡ ሰክተው ፡ ማየት ፡ በዚያን ፡ ዘመን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። የተቈረጠውን ፡ ራስ ፡ የሚመለከቱ ፡ ፊቱን ፡ እያዩ ፡ ይህ ፡ የክቡር ፡ እገሌ ፡ ይህም ፡ የወይዘሮ ፡ እገሊት ፡ ራስ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይችሉ ፡ ነበር ።

፲ ፤ በኋላ ፡ አንገታቸውን ፡ የሚሠየፉት ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የመቍረጡ ፡ ሥራ ፡ እየበዛ ፡ አልጣደፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በመኪና ፡ ለመቍረጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ዚህ ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ለዚሁ ፡ ተብሎ ፡ የተሠራ ፡ ጊሎቲን ፡ የሚሉትን ፡ መኪና ፡ አወጡ ።

፲፩ ፤ ይህም ፡ የበደለኞች ፡ መቅጫ ፡ በፈረንሳይ ፡ ትዕቢተኞች ፡ ክቡራን ፡ በካህናቱና ፡ በወይዛዝሩ ፡ ላይ ፡ እንዲሠራ ፡ ተጠመደ ፤ ስንትና ፡ ስንት ፡ የሰው ፡ ራስ ፡ በፈረንሳይ ፡ አደባባይ ፡ ወደቀና ፡ ደማቸው ፡ በጐዳና ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጎርፍ ፡ ጎረፈ ።

፲፪ ፤ የመንግሥቱ ፡ ታላላቆች ፡ አንገታቸውን ፡ ሲቈረጡ ፡ ሕዝቡ ፡ ዐይናቸውን ፡ የጣሉበት ፡ (ትኵር ፡ ብለው ፡ ይመለከቱት ፡ የነበረው ፡) ዘውድ ፡ ተሸክሞ ፡ የነበረውን ፡ ራስ ፡ ነው ። የንጉሡም ፡ ራስ ፡ ይቈረጥ ፡ እያሉ ፡ ጮሁ ። እንዲሁ ፡ ንጉሣቸውን ፡ በሕዝቡ ፡ መኻከል ፡ እየጐተቱ ፡ ወሰዱትና ፡ አንገቱ ፡ በመኪና ፡ እንዲቈረጥ ፡ ተፈረደበት ።

፲፫ ፤ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ መሰላሉ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ በጭከናና ፡ በንዴት ፡ ዙሪያውን ፡ ሁነው ፡ የሚመለከቱትን ፡ ሕዝብ ፡ አየ ። ነገሩ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሕልም ፡ መሰለው ። የገዛ ፡

ዜጎቹ ፡ ሲሞት ፡ ለማየት ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፤ መኪናውን ፡ ቢመለከት ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ በታረዱት ፡ በብዙ ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ተበከለ ፡ አየው ።

፲፫ ፤ በዚያ ፡ በመሰላሉ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ካህን ፡ ቁሞ ፡ ነበር ፤ ሌሎቹ ፡ ካህናት ፡ በነዚህ ፡ በሚያስፈሩ ፡ ቀኖች ፡ በአምላካቸው ፡ አልታመኑም ። ነገር ፡ ግን ፡ በሃ ይማኖቱ ፡ ጸንቶ ፡ የተገኘ ፡ ይኸው ፡ አንዱ ፡ ካህን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ሌሎቹ ፡ ዜጎች ፡ ንጉሣቸውን ፡ አሳልፈው ፡ ሲሰጡ ፤ በመሰላሉ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ያከበረው ፡ ይኸው ፡ ካህን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ላዘነው ፡ ንጉሥ ፡ የማጽናናት ፡ ቃል ፡ በጆሮው ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ሹክ ፡ እያለው ፡ በጣቱ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አመለከተው ። ንጉሡም ፡ በጸጥታና ፡ በትዕግሥት ፡ ራሱን ፡ ወደ ፡ መኪናው ፡ አግብቶ ፡ ሲያጋድም ፤ ካህኑ ፡ የቅዱስ ፡ ሉዊስ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ውጣ ፡ አለው ።

፲፭ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመኪናው ፡ መጥረቢያ ፡ ከላይ ፡ ሲወርድ ፡ ዘውድ ፡ የተሸከ መው ፡ ራስ ፡ ከሌላው ፡ አካል ፡ ተለየና ፡ የንጉሥ ፡ ዘር ፡ ደም ፡ እየመነጨ ፡ በመ ኪናው ፡ ላይ ፡ ተንፋዋፋዋ ። የብዙዎች ፡ ነገሥታት ፡ ኃጢአትና ፡ ያለ ፡ አገባብ ፡ የሠ ሩት ፡ የኀይል ፡ ሥራ ፡ በንጹሖቹ ፡ ልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ በቀል ፡ ያመጣል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ፲፮ኛው ፡ ሉዊስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፪ ፤ ሜሪ ፡ አንቱዋኔት ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ?
፫ ፤ የአሜሪካ ፡ ዓመፅ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ፡ ? የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?
፬ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ፈረንሳይ ፡ እንዴት ፡ ሆኖ ፡ ታየ ፡ ?
፭ ፤ በ፲፯፻፹፱ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ? ባሲቲል ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፮ ፤ ይህ ፡ የጥንቱ ፡ ምሽግ ፡ በመፍረሱ ፡ ምንድን ፡ ተደረገ ፡ ?
፯ ፡ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፡ ?
በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በፓሪስ ፡ የተለመደ ፡ ሆኖ ፡ የታየው ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ?
፱ ፤ ጊሎቲን ፡ የተባለ ፡ መኪና ፡ ያወጡት ፡ ለምን ፡ ጉዳይ ፡ ነበር ፡ ?
፲ ፤ ጥቅሙ ፡ ለምንድነው ፡ ? ያ፲፮ኛውን ፡ ሉዊስ ፡ አማሙዋት ፡ ተናገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፻፵፩ ፡ ኤውሮጳ ።

### ስለ ፤ ናፖሊዎን ፡ ቦናፓርቴ ፡ መንግሥት ።

፩፤ የንጉሡ ፡ መታረድ ፡ ጥር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ሺ ፡ ፯፻፺፫ ፡ ዓ. ም. ነበር ፤ ወዲያውም ፡ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ንግሥቲቱ ፡ ታረደች ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፈረንሳይ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ጊሎቲን ፡ በሚሰድ ፡ ባንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተገዛች ፡ ይህንም ፡ ግዛት ፡ ፈረንሳዎች ፡ ሬፑብሊክ ፡ ይሉታል ።

፱ ፤ ወዲያው ፡ ዙሪያውን ፡ በሁሉም ፡ ወገን ፡ ጦርነት ፡ ተነሣና ፡ አውስትሪያ ፤ ፕሩሲያ ፤ እንግላንድ ፤ ሆላንድ ፤ እስጴን ፡ ረሺያ ፡ ሆነው ፡ ፈረንሳይን ፡ ለመውጋት፡ጦር ፡ ሰደዱ ። ፈረንሳይም ፡ አንድ ፡ ሚሊዮን ፡ ጦር ፡ አሰናዳና፡ለኤውሮጶች ፡ ሁሉ ፡ ትምክህቱን ፡ አሳየ ።

፲ ፤ በፈረንሳይ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ናፖሊዎን ፡ ቦናፓርት ፡ የተባለ ፡ የመድፍ ፡ አለቃ ፡ (ሌፍቴናንት ፡ ) ነበር ። በብዙ ፡ ምሽግና ፡ በብዙ፡ጦርነት፡ላይ ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ እያደር፡ስሙን ፡ አስጠራው ፡ እንጂ ፤ ይህ ፡ ጦርነት ፡ በተጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ወዳጅም ፡ አልነበረውም ። እንዲሁ ፡ ቈይቶ ፡ ሳለ ፡ የጀግንነቱ ፡ ዝና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ መሰማት ፡ ጀመረ ።

፲፩ ፤ የ፲፯፻፺፮ ዓመት ፡ ጕበዝ ፡ ሳለ ፡ ጣልያንን ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ ያዘው ። በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ የአውስትርያን ፡ ንጉሥ፡ዕርቅ ፡ እንዲያደርግ፡አስገደደው ፡ በሺ፡፯፻፺፰ ፡ ግብፅን ፡ ወረረ ። በፒራሚዱ ፡ መኻከልና ፡ ባሸዋው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዋጋ ።

፲፪ ፤ የመንግሥታቸው ፡ መኪና ፡ ጊሎቲን ፡ ብቻ ፡ በሆነው ፡ ሰዎች ፡ መገዛትን ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ ሰለቸው ፡ (ጊሎቲን ፡ ) ያመፀኞችን ፡ አንገት ፡ የሚቈርጡበት ፡ መኪና ፡ ነው ፤ ሕዝቡ ፡ የሚፈልጉት ፡ ገዢ ፤ አንገታቸውን ፡ በሚቈርጥ፡መኪና፡ ማስፈራራት ፡ ሳይሆን ፡ በፈቃዳቸው ፡ በትሕትና ፡ የሚታዘዙለት ፡ ገዢ ፡ ነበር ።

፲፫ ፤ ናፖሊዎን፡ ቦናፓርት ፡ የራሱን ፡ ጥቅምና ፡ ከንቱ፡ክብርን፡ፈላጊ ፡ ነበረ፡እንጂ፡ ደግ ፡ ወይም፡ብልህ ፤ ሰው፡የሚሉት፡አልነበረም ። ምንአልባት፡ እንደ፡ፈረንሳይ፡ ላለ ፡ ሕዝብ ፡ የሚስማማ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

፲፬ ፤ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ፡ልባቸው ፡ ያላረፈ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ፡ሆኑ ፡ አስተውሎ፡ ‹እነርሱን ፡ እልክ ፡ ለማግባት፡ምናልባት ፡ ችግር፡ሳይሆን፡አይቀርም ። እርስ፡በርሳቸው፡ ከመተራረድ ፡ እየተያዙም ፡ በመኪና ፡ ተመቈረጥ ፡ ይልቅ ፡ ከውጭ ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ መዋጋት፡ይሻላቸዋል ፡ ›ብሎ፡አሰበ ። ይህንንም ፡ ማሰቡ፡ባንድ ፡ ወገን ፡ የማይ ሆንለት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ የራሱን ፡ ክብር ፡ ፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ናፖሊዎን ፡ ቦናፓርት ፡ ኀይለኛና ፡ ድል ፡ አድራጊ ፡ እንዲባል ፡ ነው ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ሉዊስ፡፲፮ኛው ፡ አንገቱን ፡ ያጣው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው፡? ስለ፡ፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ተናገር ።
፪ ፤ ከፈረንሳይ ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ የተነሡት ፡ አገሮች ፡ እነማን ፡ ናቸው፡?
፫ ፤ ናፖሊዎን ፡ ቦናፓርት ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፬ ፤ ናፖሊዎን ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ?
፭ ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የፈረንሳይ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
፮ ፤ ናፖሊዎን ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?
፯ ፤ በፈረንሳዎች ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ያስብ ፡ ነበር ፡ ? ምን ፡ ሆነ፧ ፡ ?